በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች 2008 በጀት ዓመት የሂሣብና የክዋኔ ኦዲት የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር
መ/ቤት

2010 ዓ.ም

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

ራዕይ

በ2017 ዓ.ም በአፍሪካ ካሉት ምርጥ የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤቶች አንዱ መሆን፤

ተልዕኮ

የሙያ ነፃነትን መሰረት ያደረገ ስራ ሽፋንና ጥራት ያለው ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ወቅታዊ የኦዲት አገልግሎት በመስጠት መልካም አስተዳደር ለማስፈን እና የመንግስትን የአፈጻጸም ብቃት ለማሳደግ እገዛ ማድረግ፤

እሴቶች

የቡድን ስራ= Team work
ተጠያቂነት= Accontablity
ተአማኒነት= Reliablity
ሀቀኝነት= Integrity
ቁርጠኝነት= Commitment

ምስጋና

የፊት ሽፋን ገጽ ፎቶ በመስጠት ለተባበረን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ምስጋና እናቀርባለን።

ግንቦት 22 ቀን 2009 ዓ.ም በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2008 በጀት ዓመት የሂሣብና የክዋኔ ኦዲት የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የተዘጋጀ
2010 ዓ.ም

ማውጫ

ግንቦት 22 ቀን 2009 ዓ.ም በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2008 በጀት ዓመት የሂሣብና የክዋኔ ኦዲት የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት........................1

የ2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ኦዲት ዕቅድና ክንውን..........3

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትን በተመለከተ..3

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በተከናወነባቸው መ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች...3

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች..4

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት...4

የውዝፍ ተሰባሳቢ ሂሣብ...5

የገቢ ሂሣብ...6

በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሣብ...6

መሰበሰብ ሲገባ ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሣ ሂሳብ...7

ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ 8

ተሰብስቦ በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ....................................9

ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ...10

በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች..................11

የወጪ ሂሣብ..12

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሣብ..................12

ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች..........................13

በብልጫ የተከፈለ ወጪ..............................14

የግገር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዢዎች.......................14

የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለትና በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ.........................15

በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ...16

ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ

ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ..........17
የማማከር ፈቃድ ሣይኖር ያለአግባብ ተረጋግጦ የተፈጸመ
የግንባታ ክፍያ..........17
በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ..........18
የተከፋይ ሂሣብ..........19
በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ..........19
የበጀት አጠቃቀም..........20
ከተፈቀደውና ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ 20
የንብረት አስተዳደር..........20
የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ..........22
መሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲትን በተመለከተ..........23
የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲትን በተመለከተ..........23
የክዋኔ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶችን በተመለከተ..........24
የማዕቀፍ ግዥ የኮንትራት ውል አፈጻጸምን በተመለከተ..........25
የውሃ ልማት ፈንድ ማመንጨትና ብድር አስተዳደርን በተመለከተ..........26
የኢነርጂ ብቃት (Energy Efficiency) እና ቁጠባ
(Energy Conservation) አፈጻጸም..........27
የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ እና የውሃ ሀብት
አስተዳደር አፈጻጸም..........29
የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ አፈጻጸምን በተመለከተ..........31
ለሥራ ተቋራጮች ለሚሰጠው ፈቃድና ቁጥጥር ቀልጣፋና ውጤታማ
የሆነ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን በተመለከተ..........32
የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ዕቅድ አፈፃፀም፣ የግንባታ እና ሌሎች
ግብዓቶች ለማሟላት የታቀደው ዕቅድ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና
ስኬታማ መሆኑን በተመለከተ..........33
በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የወረዳ ኔት አፈፃፀም..........33
ለአካል ጉዳተኞች የሚደረገው ድጋፍና ክትትልን በተመለከተ..........34
በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የጉምሩክ ስነ ሥርዓት አፈጻጸም..........35
በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የደንበኞች አገልግሎት
አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማነትን በተመለከተ..........36
የእንስሳት መድኀኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አፈፃፀምን በተመለከተ..........38
የማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታ በተገባው ውል መሰረት መከናወኑን በተመለከተ..........38
በስኳር ኮርፖሬሽን የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ሥራዎች

ውጤታማነትን በተመለከተ..........40
የልዩ ኦዲት ስራዎች..........40
በመ/ቤታችን በተሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦች ላይ የማስተካከያ
እርምጃ ስለመወሰዱ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ..........41
የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ..........42
ሴክተር ዘለል ሥራዎችን በተመለከተ..........43
የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በተመለከተ..........43
የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሁኔታ..........44
የ2008 በጀት ዓመትና 2009 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር የበጀት አጠቃቀም..........45
መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች..........45
የ2009/2010 ኦዲት ዓመት ዕቅድ..........46
በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች
የተከናወነ ኦዲት..........46
ኦዲት የተደረጉ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች የሂሣብ መግለጫዎች
ላይ የተሰጠ የኦዲት አስተያየት..........47
የኮርፖሬሽኑ የዕቅድ ክንውን..........48
የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ አንቅስቃሴ..........48
ማጠቃለያ..........49
አባሪ-1 ሀ/ ሂሳባቸውን በወቅቱ ያልዘጉና ዘግይተው ለኦዲት ያቀረቡ መ/ቤቶች
በ2008ና ባለፉት ሶስት ኦዲቶች ሂሣባቸው የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ
ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸው/X/ ወይም አስተያየት
ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች/XX/..........54
አባሪ 2 የ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት ማሻሻያ ሀሳብ አተገባበር
የድርጊት መርሃ ግብር እስከ ሚያዝያ 30/2009 የላኩ እና
ያልላኩ መ/ቤቶች..........58
አባሪ 3 የ2008/9 ኦዲት ዓመት የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት የመርሃ ግብር እስከ
ሚያዝያ 30/2009 የላኩ እና ያልላኩ መ/ቤቶች ዝርዝር..........61
አባሪ 4 የ2008/9 ኦዲት ዓመት የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት የመርሃ ግብር
እስከ ሚያዝያ 30/2009 የላኩ እና ያልላኩ መ/ቤቶች ዝርዝር 66

ግንቦት 22 ቀን 2009 ዓ.ም በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2008 በጀት ዓመት የሂሣብና የክዋኔ ኦዲት የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት

- **የተከበሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ፤**
- **የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔ፤**
- **የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፤**
- **ክቡራትና ክቡራን፤**

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀፅ 2 እና መሥሪያ ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 አንቀጽ 5 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 15፤ እንዲሁም በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ኦዲት ያደረጋቸውንና ያስደረጋቸውን የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርት፣ በመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ (Protection of Basic Services) ፕሮግራም አማካይነት የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግሥታት የሰጠውን የበጀት ድጋፍና ድጎማ ተከታታይ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች፤ የመንግሥት መ/ቤቶች አሠራር ህጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ፤ ተፈላጊውን ግብ የመታና ውጤት ያስገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገውን የክዋኔና አካባቢ ኦዲት፣ እንዲሁም ስለመ/ቤቱ አጠቃላይ ሥራዎች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ዓመታዊ ሪፖርት እንደሚያቀርብ በተደነገገው መሠረት የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲትና በተመረጡ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲቶች ዕቅድ ክንውንና የኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት፤

1. በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ ላይ የተከናወኑ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት እና በመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮግራም ለክልሎች የተሰጠ ድጋፍ (Protection of Basic

Services III) ተከታታይ እና ማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች ናቸው፡፡

2. ሪፖርቱ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ፈቃድ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት የተደረጉትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሂሳብና በመንግስትና ልማት አጋር ድርጅቶች እርዳታና ብድር የሚካሄዱ ፕሮጀክቶችን/ፕሮግራሞችን ኦዲት ያካትታል፡፡

3. የ2008/9 ኦዲት ዓመት የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሣብ የኦዲት ዕቅድ ክንውን እና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣ የመሥሪያ ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ፣ በኦዲት ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን አጭር የሥራ እንቅስቃሴን ያጠቃለለ ነው፡፡

4. የ2008 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ በመ/ቤታችን የተከናወኑ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርቶች ራሳቸውን ችለው በተጠናቀሩ 2 ጥራዞች፣ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው 5 መ/ቤቶችና የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው 53 መ/ቤቶች፣ እንዲሁም የ18 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችና የ7 ክዋኔ ኦዲት የክትትል ኦዲት ለምክር ቤቱ የቀረቡ ስለሆነ እነዚህን ሪፖርቶች የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በሚገባ በመመርመር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል በጥልቀት ተዘጋጅቷል፡፡ የሪፖርቶቹ ቅጅ በ2 ጥራዞች /የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርት እና አጠቃላይ ዘገባ/ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤትም /በሶፍት ኮፒ/ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

5. እያንዳንዱ የኦዲት ሥራ እንደተጠናቀቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በኦዲቱ ግኝቶች ላይ የመውጫ ስብሰባ (Exit Conference) ከመደረጉም ሌላ ረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት ተልኮላቸው መ/ቤቶቹ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ የሰጡትን ምላሽ ያገናዘበ በመሆኑ የመረጃዎቹ ተአማኒነትና አግባብነት በሁሉም ወገን ተቀባይነት እንዳለው ይታመናል፡፡

6. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ዓለም አቀፍ የመንግሥት የኦዲት ደረጃዎች፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ሲሆኑ ኦዲቱም የተከናወነው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነትና አግባብነት ሙሉ በሙሉ ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የ2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ኦዲት ዕቅድና ክንውን

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትን በተመለከተ

7. የ2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ ኦዲት ዕቅድ መሠረት ያደረገው የመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ 982/2008 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1-15ን እና የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 አንቀጽ 63/2ን (በአዋጅ 970/2008 እንደተሻሻለው) ነው፡፡ በየዓመቱ የኦዲት ሥራ የሚጀመረው በመጋቢት ወር ሲሆን አስቀድሞ በየካቲት ወር ዕቅድ በማዘጋጀትና በኦዲት ማኑዋሎች በተደረጉ ለውጦች ላይ ሥልጠና በመስጠት የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሳባቸውን መዝጋታቸውን ሳንጠብቅ ኢንትሪም የኦዲት ዘዴን በመጠቀም ኦዲቱን መጋቢት 2008 በመጀመር ጥር 30/2009 ዓ.ም ለማጠናቀቅ ታቅዶ ነበር፡፡

8. በዚሁ መሠረት በ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 165 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል 158 መ/ቤቶችንና 48 ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶቻቸውን በመ/ቤታችን አማካይነት፣ የተቀሩትን ሰባቱን ደግሞ በኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን ኦዲት በማስደረግ የኦዲት ሽፋኑን 100% ለማድረስ የታቀደ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመ/ቤታችን በኩል ኦዲት ለማድረግ ከታቀዱት 158 መ/ቤቶች የሁሉም ኦዲት (ከ44 ቅ/ጽ/ቤቶች ጋር) የተጠናቀቀ ከመሆኑም በላይ የፌዴራሉ መንግሥት የ2008 በጀት ዓመት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲትም በመከናወኑ በአጠቃላይ የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ዕቅድ አፈጻጸም 100%፣ የኦዲት ሽፋኑንም 100% ቀጣይነት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በተከናወነባቸው መ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች

9. የ2008 በጀት ዓመት ሂሣብን በተመለከተ መ/ቤታችን በ158 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች ላይ ኦዲት በማድረግ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለየመ/ቤቶቹ የላከ ሲሆን፣ የባለበጀት መ/ቤቶቹ ሪፖርቶችም ከግኝታቸው ባሕርይ አንፃር ከ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መግለጫ /የተሰጠው የኦዲት አስተያየት/	ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት	
	የተሰጠው የኦዲት አስተያየት	ኦዲት የተደረጉ
ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት	36	27
ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው የተገኙ	66	73
አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች	6	5
የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው	37	53
ሂሳባቸውን በወቅቱ ስላልዘጉ ኦዲት ያልተደረጉ	1	-
ድምር	145	158

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች

10. መ/ቤታችን ምክር ቤቱ ያጸደቀው በጀት የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ፣ ደንብና መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ በ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ ባከናወነው ኦዲት በርካታ የሂሳብ አያያዝ ግድፈቶች እና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች፣ እንዲሁም አፈጻጸማቸው ከደንብና መመሪያ ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች የተገኙ ሲሆን፤ የምክር ቤቱን ትኩረት ሊያገኙ ይገባል ተብሎ የታመነባቸው አንኳር ግኝቶች ብቻ ተለይተው እንደሚከተለው ቀርበዋል::

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

11. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝና አጠባበቅ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በአዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 144,716.56 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል።

12. በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል በ5 መ/ቤቶች (በአዲስ አበባ ኤርፖርት ገ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት፣ በጅግጂጋ ዩኒቨርሲቲ፣ በጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ፤ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) ቆጠራው ከመዝገብ ጋር ሲነፃፀር በብር 379,390,668.85 በማነስ ልዩነት የታየ ሲሆን፣ በ2 መ/ቤቶች (በሀዋሣ ዩኒቨርሲቲ እና በዲላ ዩኒቨርሲቲ) ደግሞ በብር 2,445,827.16 ቆጠራው ከመዝገብ በመብለጥ ታይቷል። እንዲሁም በ20 መ/ቤቶችና በ4 ቅ/ጽ/ቤቶች የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች መኖራቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል።

13. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳቦች ላይ ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ብክነት፤ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፤ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር፤ በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በቆጠራ ከተገኘው ጋር ሲመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ፤ በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተገቢው እርምጃ ተወስዶ እንዲተካ፣ በማነስ/በመብለጥ የታየው ልዩነትም ተጣርቶ እንዲተካ ወይም ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ እና የታዩት የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንዲስተካከሉ አሳስበናል።

የውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ

14. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እስከ 35 በተደነገገው መሠረት የሰነድ ሂሳብ በወቅቱ መወራረዱ ሲጣራ በ113 መ/ቤቶችና በ28 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 5,262,275,550.73 በደንቡ መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል። ከዚህ ውስጥ ብር 375,557,284.38 በ6 መ/ቤቶች እና 6 ቅ/ጽ/ቤቶች ከመቼ ጀምሮ በተሰብሳቢነት እንደተመዘገበ፤ ከማን እንደሚሰበሰብ በቂ ማስረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ሂሳብ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል።

15. በወቅቱ ያልተወራረደው ተሰብሳቢ ሂሳብ በዕድሜ ወይም በቆይታ ጊዜው ሲተነተን ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 134,153,964.72፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 3,174,764,464.42፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 372,936,870.76 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 196,565,227.12 ሲሆን ቀሪው ሂሳብ ብር 1,442,465,210.85 የቆይታ ጊዜ በግልጽ ለመለየት አልተቻለም።

16. ከዚህ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት

የብሔራዊ አደጋ ስጋትና ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 2,388,942,192.66፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 720,059,425.92፣ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 461,024,828.37፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 352,267,320.48፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 172,017,623.31፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ብር 122,357,333.28፣ በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴርና በሥሩ ባሉት 7 ተጠሪ ተቋማት ብር 120,806,110.43፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ብር 119,048,306.24፤ የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ብር 108,320,687.31፤ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 82,078,962.89፣ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር እና ሶስት ተጠሪ ተቋማት ብር 57,915,537.72 እና ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 55,650,002.47 ይገኙበታል።

17. በተጨማሪም በሁለት መ/ቤቶች ያለአግባብ ከተሰብሳቢ ሂሳብ የተሰረዘ ብር 11,155,949.90 ተገኝቷል።

18. በመሆኑም መ/ቤቶች ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣቦቹን ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ተከታትለው ገንዘቡን እንዲሰበስቡ ወይም እንዲያወራርዱ፤ ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቀው ተጣርቶ እንዲረጋገጥና እንዲሰበሰብ ወይም እንዲወራረድ፤ ያላግባብ ከመዝገብ የተሠረዘው ተመልሶ በተሰብሳቢነት እንዲተከል አሳስበናል።

የገቢ ሂሣብ

19. የመንግሥት ገቢ በወጡት ሕጎች መሰረት በአግባቡ መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል።

በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሣብ

20. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች፤ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት እና በስሩ ባሉ አስራ አምስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ብር 1,137,991,342.68፣ በሌሎች በ30 መ/ቤቶች ብር 5,920,743.20 በድምሩ ብር 1,143,912,085.88 ገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስን እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ ህጎች መሠረት ሳይሰበሰብ ተገኝቷል።

21. በአዋጁ መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች መካከል በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ብር 725,157,433.77፣ የአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 239,105,787.51፣ የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 55,660,066.90፣ አዲስ አበባ ኤርፖርት ገ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት ብር 42,602,011.26፣ የኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 20,474,305.24፣ የጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 19,595,253.19 ሲሆን ከሌሎች መ/ቤቶች ደግሞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ብር 2,334,379.40 እና የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ብር 1,512,791.25 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

22. የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ ሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S.Code) እና Custom Procedure Code (CPC Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በትክክለኛው የትራንስፖርት የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የኢንሹራንስና ሌሎች ወጪዎች ለቀረጥ ማስከፈያነት ባለመወሰዳቸው ምክንያት ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር፣ በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ እቃዎች ላይ በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ ያለፈበት ቢሆንም በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያልተደረገ በመሆኑ እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (withholding tax)፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

23. በመሆኑም መ/ቤቶቹ ለወደፊቱ የመንግሥትን ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸውና በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

መሰብሰብ ሲገባው ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሣ ሂሳብ

24. በፌዴራል መንግሥት የግዢ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4 (ሀ) እና (ለ) መሠረት አቅራቢው ሣይፈጽም በቀረው የውል

መጠን ላይ ውል ሰጪ የመንግሥት መ/ቤቶች በየቀኑ 0.1% ወይም 1/1000ኛ ከውሉ ዋጋ 10% ሣይበልጥ የጉዳት ካሣ ሊሰበስቡ እንደሚገባ ያመለክታል። በዚህ መሠረት መ/ቤቶች በውሉ መሠረት ባልፈጸሙት አቅራቢዎች ወይም አገልግሎት ሰጪዎች ላይ በመመሪያው መሠረት ተገቢውን እርምጃ የወሰዱ መሆኑ ሲጣራ በ19 መ/ቤቶች ከህንጻ ስራ ተቋራጮችና ዕቃ አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ያልሰበሰቡት የጉዳት ካሣ ወይም ቅጣት ብር 226,318,955.97 ተገኝቷል።

25. በተጨማሪም በተፈረመው የውል ስምምነት መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢና ቅጣት በ3 መ/ቤቶች ብር 6,157,838.84 እና በሁለት መ/ቤቶች ደግሞ የገንዘብ መጠኑ ያልተገለጸ ገቢ በውሉ መሰረት ያልተሰበሰበ ሂሳብ ተገኝቷል።

26. የጉዳት ካሣውን ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 44,825,207.62፣ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,399,294.00፤ አክሱም ዩኒቨርሲቲ ብር 23,795,857.19፤ ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ብር 23,015,018.98፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 19,782,858.73፣ ዲላ ዩኒቨርስቲ ብር 9,701,565.92 እና አምቦ ዩኒቨርሲቲ ብር 8,527,962.55 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

27. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በተቀመጠው መመሪያ መሠረት እስከ አሁን ያልተሰበሰበውን ገቢና የጉዳት ካሣ እንዲሰበስቡና ለወደፊቱም መመሪያው በሚጠይቀው መሠረት እንዲፈጽሙ አሳስበናል።

ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

28. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዘጠኝ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በሌሎች 5 መ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፤ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው በድምሩ ብር 4,009,579,782.80 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ታውቋል። በሌላ በኩል በግብር ከፋዮች ለቀረበው ቅሬታ አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴው በወቅቱ ውሳኔ ባለመስጠቱ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤትና በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ በወቅቱ ያልተሰበሰበ በድምሩ ብር 3,534,374,123.04 ውዝፍ የግብር፤ ቀረጥና ታክስ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል። በተጨማሪም በ3 መ/ቤቶች ከሰጡት የዱቤ ሽያጭ አገልግሎት ያልተሰበሰበ ብር 758,441,552.94

ውዝፍ የዱቤ ሽያጭ ሂሳብ መኖሩ በኦዲቱ ተረጋግጧል።

29. ውዝፍ ገቢን በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት ብር 621,050,644.38 (ከተወረሱ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ሽያጭ እስከ 8 ዓመታት የቆየ)፣ በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 3,568,784,786.96፤ የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 221,873,831.48፤ የድሬዳዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 82,614,496.40፤ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ብር 53,030,155.76፣ የምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 49,103,485.09 እና የባህር ዳር ገ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት ብር 36,468,864.32 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

30. በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት የሚያከናውናቸውን ማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማት አገልግሎቶችን ለማስፋፋትና መሠረተ ልማትን ለመዘርጋት እንዲሁም ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ መሳካት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ፤ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶ የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል።

ተሰብስቦ በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ

31. በበጀት ዓመቱ ገቢን እንዲሰበስቡ በተፈቀደላቸው የመንግሥት መ/ቤቶች የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ11 መ/ቤቶች ብር 196,400,089.47 እና በሌሎች ሁለት መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ የሰበሰቡት የውስጥ ገቢ ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል። በ5 መ/ቤቶች ብር 8,250,112.36 ከተለያዩ ገቢዎችና ከሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ የቀረውን ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ወይም ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ/ ያልተደረገ ሂሳብ ተገኝቷል።

32. የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱት መ/ቤቶች አሁንም አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ ይህ አሰራር በገቢ ሂሳብ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ለምዝበራ በር የሚከፍት ከመሆኑም በላይ መ/ቤቶቹ በራሳቸው የሚያዘጋጁቸው የሂሳብ መግለጫዎችና የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብም ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ያደርጋል።

33. በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቡትን ማንኛውንም የመንግስት ገቢ ሕጋዊ በሆነ መንገድ በመሰብሰብ እንዲመዘግቡና በሂሳብ መግለጫዎቻቸው

በማካተት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት በማድረግ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡ በዚህ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በማይወስዱ፣ የመንግሥትን ገቢ ሰብስበው መዝገብ የማይዙና የሚደብቁ መ/ቤቶች ላይ መንግሥት ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

34. የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አምስት ቅ/ጽ/ቤቶች እና በ8 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 36,807,405.88 እና በሌሎች 6 መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ ማስረጃዎች ባለመሟላታቸው የገቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በሌላም በኩል በናሙና ከታዩት ፋይሎች ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር ያላሳወቁ 119 ግብር ከፋዮች፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቁ 27 ግብር ከፋዮች እና ኤክሳይስ ታክስና ተርንኦቨር ታክስ ያላሳወቁ 11 ግብር ከፋዮች የተገኙ ሲሆን የሚፈለግባቸው ግብር ሂሳብ ምን ያህል እንደሆነም፤ ግብሩንም ስለመክፈላቸው/ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም ገቢ የተሰበሰበባቸው 170 ዲክላራሲዮኖች ለኦዲት ተጠይቆ ያልቀረቡ በመሆኑ በነዚህ ዲክላራሲዮኖች የተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

35. በተጨማሪም አግባብ ባለው አካል የጸደቀ የገቢ ታሪፍ /የማስከፈያ ተመን/ ባለመኖሩ፣ የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፣ ገቢው ከምን አይነት አገልግሎት እንደተሰበሰበ የሚገልጽ ደጋፊ ማስረጃ ከገቢ ደረሰኞቹ ጋር ያልተያያዘ በመሆኑ፤ የውስጥ ገቢ ሂሳብ ምዝገባ ባለመካሄዱ እና የውስጥ ገቢ የፋይናንስ እንቅስቃሴን የሚገልጹ አግባብነት ያላቸው የሂሳብ ሪፖርቶች እና መግለጫዎች ባለመዘጋጀታቸው እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የገቢ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

36. ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ የገቢ ማስረጃዎች ዝርዝር በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ፤ ግብር ከፋዮች የሚፈለግባቸውን ግብር በሙሉ በወቅቱ አሳውቀው እንዲከፍሉ ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች

37. በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

38. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 መሰረት የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አፈጻጸምን ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 118/2008 አንቀጽ 15(1-5) እንዲሁም በብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2008 ክፍል 5 ቁጥር 18(2) መሰረት ማንኛውም መንገደኛ ወደ ሀገር ሲገባ የያዘው የውጭ ምንዛሪ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ከተፈቀደው መጠን በላይ ከሆነ ባለስልጣኑ ባዘጋጀው ዲክላራሲዮን ላይ መመዝገብ እንደሚኖርበት እና ተመልሶ ለመውጣት ሲፈልግ ገንዘቡን ያስመዘገበበትን ዲክላራሲዮን ካላቀረበ በስተቀር መልሶ ለማውጣት እንደማይችል የሚገልጽ ቢሆንም በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በውጭ ዜጎች ባለቤትነት በቀን 22/05/2008 የውጭ ምንዛሪ በዩሮ 211,220.00 እና በዶላር 1,700.0 በወቅቱ ባለው የሀገር ውስጥ ምንዛሬ ሲመነዘር ብር 4,876,186.20 እና 4.336 ኪ.ግ ወርቅ የግለሰቡ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሳይኖር እና የገንዘቡ ህጋዊነት በአግባቡ ሳይረጋገጥ ለግለሰቡ እንዲመለስ የተደረገ መሆኑን፣

39. በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀፅ 30 ንዑስ አንቀፅ 2(ሀ) እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀፅ 13 ላይ የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ስለመሆን በሚለው ከንዑስ አንቀፅ 1-4 በተዘረዘሩት መሰረት የኢንቨስትመንት የቀረጥ ነፃ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አሰራር ላይ ክትትል እየተደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት እያንዳንዱ አስመጪ ድርጅት ከቀረጥ ነፃ ዕቃዎችን በሚያስገባበት ወቅት የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ የተጠቀሱት ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ደብዳቤውን በቀጥታ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚጽፍ መሆኑ በዋና መ/ቤት የሚገኘው የኢንቨስትመንት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት አውቆት ክትትል የማይደረግበት መሆኑ፣

40. አስመጪ ድርጅቶች ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ሲጀምሩ በሚያስገቡበት የጉምሩክ ጣቢያ ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሊያስገቡ የተፈቀደላቸውን የዕቃዎች ብዛትና ዓይነት ለማወቅ የሚያስችል አሰራር

ያልተዘረጋ መሆኑ ታውቋል፤

41. በመሆኑም የመንግስት ገቢ የገቢ አዋጆች፤ ደንብና መመሪያዎችን መሰረት እንዲከናወንና ለታዩትም ድክመቶች አስፈላጊውን ማስተካከያዎች በማድረግ ገቢው እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

የወጪ ሂሣብ

42. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መሠረት በአግባቡ ወጪ ማድረጋቸውና መጠቀማቸውን፣ ተገቢው ማስረጃ መቅረቡንና ሂሣቡም በትክክል መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሣብ

43. በወጪ ለተመዘገቡ ሂሣቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ59 መ/ቤቶች ብር 236,452,502.91 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

44. የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል ጅማ ዩኒቨርሲቲ ብር 47,697,409.60፤ የአሶሳ ዩኒቨርስቲ ብር 25,870,747.59፤ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 21,125,500.00፤ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ብር 20,951,955.77 እና አርሲ ዩኒቨርሲቲ ብር 20,538,683.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

45. ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚያሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፤ የመንግሥት ሰራተኞች የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ አንድ ሳይዘጋጅ፣ ለስልጠና መስተንግዶ ለተከፈለው ሂሳብ መስተንግዶውና ስልጠናው በትክክል ለመሰጠቱ የሰዓት ፊርማ (አቴንዳንስ) በማስረጃነት ሳይቀርብ እና በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ሳይረጋገጥ፤ የቀረቡት ተራ ደረሰኞች ማለትም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሌላቸው እና በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን ወይም ለተቀባዩ ስለመድረሱ የሚገልጽ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጉላ ያሉት ናቸው፡፡

46. ማንኛውም ሂሣብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ማስረጃዎች መሟላታቸው እንዲረጋገጥ፣ ያልተሟሉት ማስረጃዎች እንዲሟሉና ለወደፊቱም

ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

47. ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ክፍያ መፈጸሙ ሲጣራ በ91 መ/ቤቶችና 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 98,768,151.60 ከደንብና መመሪያ ውጭ አለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

48. ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ብር 16,626,212.78፣ ደብረታቦር ዩኒቨርስቲ ብር 13,324,499.96፣ ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ብር 10,149,481.18፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,279,127.30፤፣ ወላይታ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,845,492.87፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,544,216.00 እና ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,880,610.00 ሲሆኑ ምክንያቶቹም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በመፈጸም፣ ለሠራተኞች አበልና ደመወዝ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ በመፈጸም፤ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈል፣ ለውጭ ጉዞ ከወሰዱት የውሎ አበል ሂሳብ በመመሪያው መሰረት መመለስ ሲገባቸው ተመላሽ ያለማድረግ፤ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የኃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ክፍያ መፈጸም፤ መ/ቤቱን ለለቀቁ ሰራተኞች ለበርካታ ወራት የደመወዝ ክፍያ መፈጸምና በሚመለከተው አካል ያልተፈቀደና ግልጽ የሆነ መስፈርት በሌለው ሁኔታ ለሰራተኞች ማበረታቻ በመክፈልና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

49. በሌላ በኩል የስራው ባህሪ ቋሚ ወይም ቀጣይነት ያለው መሆኑ እየታወቀ በፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ያልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች ቅጥር በመፈጸም በ8 ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተፈጸመ የብር 7,633,947.38 የደመወዝ ክፍያ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም በሌሎች 11 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደግሞ ተመራማሪዎች ጥናት ላቀረቡበት፣ ለፈተና ግምገማ፣ የማስተርስና ፒ.ኤች.ዲ ተማሪ ፈተና ለፈተኑበትና ለገመገሙበት ክፍያና ለመመረቂያ ጽሁፍ ማማከር ሥራዎች በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር ብር 58,364,234.32 የተፈጸሙ ክፍያዎች መኖራቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

50. በመሆኑም ከደንብና መመሪያ ውጪ ያለአግባብ የተከፈለው ሂሣብ ተመላሽ እንዲሆን፤ ለወደፊቱም ደንብና መመሪያዎች ተከብረው መሰራት እንዳለበት ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶች አሳስበናል፡፡

በብልጫ የተከፈለ ወጪ

51. በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሰረት በአግባቡ የተከናወኑ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸሙ ክፍያዎች ስለመሆናቸው ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ18 መ/ቤቶች ለግንባታና ለተለያዩ ሌሎች ግዢዎች ብር 19,512,255.86 እና በ25 መ/ቤቶች ደግሞ ለደመወዝ፣ ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 10,489,782.97 በጠቅላላው ብር 29,944,144.83 እና በ1 መ/ቤት $2,500.00 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

52. በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ሂደት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ያለበቂ ምክንያት ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፤ ከተገባው ውል ውጭ በመክፈል፤ ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል እንዲሁም ለትርፍ ሰአት፣ ለተለያየ ጥቅማ ጥቅም እና ለመኖሪያ ቤት አበል ከተፈቀደው በላይ በብልጫ የተከፈሉ ይገኙበታል፡፡

53. ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ ህግን የተከተለ ካለመሆኑም በላይ የመንግስትን ሀብት ለብክነት የሚዳርግና ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡ በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡትን ደንብና መመሪያዎች ተከትለው መፈጸም እንደሚገባቸውና በብልጫ የተከፈለውም ወጪ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆንና አስፈላጊውም እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዢዎች

54. የዕቃና አገልግሎት ግዢ በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ79 መ/ቤቶችና 4 ቅ/ጽ/ቤቶች ያለጨረታ ቀጥታ ግዥ በመፈጸም ብር 185,413,357.21፤ መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ ግዥ በመፈጸም ብር 30,659,951.58፤ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ ብር 42,915,658.54 እና ሌሎች የግዥ ሂደት ያልተከተሉ ብር 65,961,134.87 በድምሩ ብር 324,950,102.20 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

55. ከግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 69,476,518.45፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 24,606,609.47፤ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 22,809,928.86፣ ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ብር 21,294,981.03፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ብር

11,720,591.17፣ አክሱም ዩኒቨርሲቲ ብር 10,105,118.59፣ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 11,037,410.63፣ ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,109,599.15 መቱ ዩኒቨርሲቲ ብር 9,701,853.51 እና አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 8,935,793.76 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

56. ከዚህም ሌላ በ6 መ/ቤቶች የተገዙት ዕቃዎች በናሙናው መሠረት ገቢ ለመሆናቸው ሣይጣራና የተጠየቀው አገልግሎት ስለመሰጠቱ በባለሙያ ሳይረጋገጥ የብር 49,599,091.24 ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

57. የግዢ መመሪያን ሳይከተሉ ግዢ መፈጸም የህግ ጥሰት ከመሆኑም በላይ መንግሥት ተወዳዳሪ ዋጋ እንዳያገኝ የሚያደርግ እንዲሁም ለምዝበራ፣ ለጥራት መጓደልና ለግብር ስወራ ጭምር የሚያጋልጥ በመሆኑ የመንግሥት የግዢ ደንብና መመሪያን አክብረው በማይሠሩ መ/ቤቶች ላይ የተጠናከረ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለትና በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

58. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዛው ንብረት ለመ/ቤቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግበ14 መ/ቤቶች በብር 21,416,544.15 ተገዙ ተብሎ በወጪ ለተመዘገበ ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች እና በ4 መ/ቤቶች ብር 2,674,478.09 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀረብላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

59. ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ብር 6,433,032.76፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 4,743,664.81፣ የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,302,552.26፣ የዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,184,000.00 እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ብር 1,073,235.00 ለግዥ ወጪ ሆኖ ለተገዛው ዕቃና ንብረት የገቢ ደረሰኝ ካልቆረጡት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ብር 1,496,954.03 እና ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 918,758.32 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

60. ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጣው ገንዘብም ሆነ ቀረጥ ተከፍሎባቸው ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ

መንግስት ለወጣው ወጪ አገልግሎት ስለማግኘቱ ማረጋገጥ የማያስችል ከመሆኑም በላይ የተገዛውም ንብረት ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

61. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ

62. በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ በደንብና በመመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ9 መ/ቤቶች ለቅድሚያ ክፍያ በድምሩ ብር 99,645,132.99 የተፈጸመው ክፍያ በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ የቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 34,163,182.83፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 31,644,188.65፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል ብር 15,925,278.41 እና የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን ብር 11,610,351.95 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

63. በሌላ በኩል በ20 መ/ቤቶች ለግንባታ ፕሮጀክቶች ከተሰጠው የቅድሚያ ክፍያ ከእያንዳንዱ የክፍያ ሠርተፊኬት እየተቀነሰ ለመንግሥት ተመላሽ ሊሆን የሚገባ ብር 133,631,062.49 ክፍያ ከተፈጸመባቸው ክፍያ ሠርተፊኬቶች ተቀናሽ ሳይደረግ የቀረ ሂሳብ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

64. ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ሲሟላ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለባቸው፡፡ የግንባታ ክፍያዎች በሚከፈሉበት ጊዜም ቀደም ሲል የተሰጠው ቅድሚያ ክፍያ እየተጣራ በሕጉ መሰረት ከእያንዳንዱ የክፍያ የምስክር ወረቀት ተቀንሶ ለመንግሥት ተመላሽ ሊሆን ይገባል፡፡ ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ በወጪነት የሚመዘገብ ቅድሚያ ክፍያ ይቅርና በተሰብሳቢነት የተያዘውም የክፍያ ሥርዓቱ ባስቀመጠው መሠረት ተቀንሶ ተመላሽ እየተደረገ ባለመሆኑ የመንግሥት ገንዘብ ባክና እንዳይቀር ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

65. በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፤ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብለት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብና ተቀናሽ ያልተደረገው ቅድሚያ ክፍያ ተጣርቶ ለመንግስት ተመላሽ እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ

66. በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ15 መ/ቤቶች ብር 36,725,016.96 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበና ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

67. ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ውስጥ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ብር 12,660,000.00፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ብር 8,179,060.00፣ የዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,873,851.63፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 4,366,013.47፣ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ብር 2,359,106.93 እና የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት ብር 2,276,002.43 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

68. ተገቢው ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ የመንግስት ገንዘብን ለጥፋትና ለብክነት የሚዳርግ በመሆኑ ለወደፊቱም ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ፣ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ በቂ ማስረጃ እንዲቀርብለት፣ አለበለዚያ ገንዘቡ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የማማከር ፈቃድ ሣይኖር ያለአግባብ ተረጋግጦ የተፈጸመ የግንባታ ክፍያ

69. ማንኛውም ግንባታ ሲከናወን ሥራው በትክክል ስለመሠራቱ ብቃቱ ተረጋግጦ የማማከር አገልገሎት እንዲሰጥ በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ፈቃድ በተሰጠው አማካሪ ድርጅት ሲረጋገጥ ብቻ ክፍያዎች ሊፈጸሙ ይገባል፡፡ ሆኖም የግንባታ ፕሮጀክቶችን ሥራ እንዲከታተሉ በየከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተቋቋሙ ነገር ግን የማማከር

ፈቃድ በሌላቸው የግንባታ ጽ/ቤቶች የክፍያ ሠርተፊኬት ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና የመሳሰሉት ሥራዎች በማከናወን በ8 መ/ቤቶች ብር 260,989,864.26 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

70. በሌላም በኩል በ3 የተለያዩ መ/ቤቶች የተጨማሪ ሥራ ውል ሥምምነት ያልተፈረመ ብር 66,383,236.25 እንዲሁም ተጨማሪ ውል ለማድረግ በህግ ከተፈቀደው የዋናው ውል 25% በላይ የግንባታ ሥራ ውል የተገባበት በ9 መ/ቤቶች ብር 140,384,732.80 በድምሩ በብር 206,767,969.05 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሳይታደስ፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከግንባታ ክፍያው ላይ ሳይቀነስ፤ የውል ሰነድ እና የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች የሚያሳይ ዝርዝር ሁኔታ ሳይቀርብ እንዲሁም የግንባታ የክፍያ ምስክር ወረቀት ሳይኖር በ5 መ/ቤቶች ብር 37,909,666.37 ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ እንደዚሁም በ3 መ/ቤቶች ሂሳቡ አስቀድሞ በተከፋይነት ሳይመዘገቡ ብር 23,130,699.31 የመያዣ ሂሳብ መከፈሉ ተረጋግጧል፡፡

71. ስራው በዲዛይኑና በተገቢው ጥራት ስለመሠራቱ የሚሰጠው ማረጋገጫ በገለልተኛና በህግ አግባብ ዕውቅና በተሰጠው አካል ካልተፈጸመ የተከናወነውን ግንባታ አስመልክቶ ችግር ቢፈጠር ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ስለማያስችል መ/ቤቶቹ እየተከተሉት ያለው አሠራር በፍጥነት እንዲቋረጥና ለግንባታዎች ተገቢው ዕውቅና ያለው አማካሪ ድርጅት እንዲቀጠር ቀደም ባሉት ዓመታትም በተደጋጋሚ ብናሳስብም አሠራሩን ለማረም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በምክር ቤቱ በኩል ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

72. ከውስጥ ገቢ እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸው ያወጡትን ወጪና ሌሎች መ/ቤቶችም የተከፈለውን ገንዘብ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት አካተው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚያቀርቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ12 መ/ቤቶችና ሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 176,427,854.32 እንዲሁም በአንድ ዩኒቨርሲቲ እና በአንድ ሆስፒታል የገንዘብ መጠኑ ያልተገለጸ ከውስጥ ገቢ የተከፈለና የሌሎች ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ ወይም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡

73. ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ የገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ እንዲሆን ከማድረጉም በተጨማሪ የመ/ቤቶቹ ትክክለኛ የፋይናንስ አፈጻጸምና ገፅታ እንዳይታወቅ ያደርጋል፡፡

74. ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ባለፉት ዓመታት ሪፖርታችንም በተደጋጋሚ እንደተገለፀው በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 (970/2008 እንደተሻሻለው) በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት ብናሳስብም በአንዳንድ መ/ቤቶች ሊታረም ባለመቻሉ ምክር ቤቱ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የተከፋይ ሂሣብ

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

75. በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ73 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,880,499,977.09 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ በ8 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች የቆይታ ጊዜውና ለማን እንደሚከፈል የማይታወቅ በመሆኑ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ብር 833,811,806.31 ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

76. የተከፋይ ሂሳቡ በዕድሜ /በቆይታ ጊዜው/ ሲተነተን ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 104,587,943.58፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 374,727,888.39፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 20,043,052.99 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 23,675,570.61 ሲሆን ቀሪው ሂሳብ ብር 1,357,278,582.92 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ለመለየት አልተቻለም፡፡

77. በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች መካከል የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 419,956,203.21፣ የምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 308,074,556.05፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ብር 285,468,377.01፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 159,561,189.14፤ የጎንደር ዩኒቨርስቲ ብር 79,227,247.16፣ የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 42,950,209.55 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

78. በመሆኑም የተመለከተው ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ ተጣርቶ በፋይናንስ ሕጉ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲከፈል፤ ትክክለኛነቱን ማጣራት ያልተቻለውም ለማን እንደሚከፈል ተጣርቶ ሊታወቅና ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የበጀት አጠቃቀም

ከተፈቀደውና ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ

79. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት በ52 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸውና ከተደለደለው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱና በጀት ሳያዛውሩ ከመደበኛ በጀት ብር 177,327,518.45 እና ከካፒታል በጀት ብር 92,432,012.04 በድምሩ ብር 269,759,530.49 ከበጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

80. ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱና ሳያዛውሩ ሥራ ላይ ካዋሉት መ/ቤቶች መካከል ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 83,491,831.42፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 46,964,205.09፣ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ብር 15,798,465.73፣ አርሲ ዩኒቨርሲቲ ብር 13,212,410.76፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 12,013,561.17 እና ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,793,868.48 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

81. በጀት ሳይፈቀድ ወይም ዝውውር ሳይደረግ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ በመሆኑ መ/ቤቶች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ እንደዚሁም በበጀት አዋጁ መሠረት የተፈቀደላቸውን በጀት የተቀመጠውን አሠራር በመከተል በተገቢው መንገድ የበጀት ዝውውር በማድረግ አስፈቅደው ሥራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡ ነገር ግን ይህ ጉዳይ እየተሻሻለ ባለመሆኑ ምክር ቤቱና የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተገቢውን አፋጣኝ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

የንብረት አስተዳደር

82. መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው የዕቃና ንብረት አስተዳደር በዚህ ዓመትም በሚፈለገው ደረጃ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ፣

ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	38 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር በማመሳከር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	39 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	19 መ/ቤቶች
ቋሚ ዕቃ መዝገብ /ስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ	17 መ/ቤቶች
የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	12 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	28 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	72 መ/ቤቶችና 14 ቅ/ጽ/ቤቶች
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	22 መ/ቤቶች
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	10 መ/ቤቶች
በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸው 243 የተለያዩ ተሽከሪካሪዎችና 11 ሞተር ብስክሌቶች	10 ቅ/ጽ/ቤቶች
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ 26 ላፕ ቶፖች እና ሌሎች ንብረቶችን ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ ያላደረጉ	2 መ/ቤቶች
የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነትን የማያረጋግጡ	4 መ/ቤቶች
በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሳይደረጉ ንብረት ክፍል የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው መ/ቤቶች	6 መ/ቤቶች
ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች	17 መ/ቤቶችና 2 ቅ/ጽ/ቤቶች

መሆናቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

83. በመሆኑም የየመ/ቤቶቹ የንብረት አስተዳደር መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲመራና በታዩት ድክመቶች

ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው በላክንላቸው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ

84. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ27 መ/ቤቶች	170 ተሽከርካሪዎችና 14 ሞተር ብስክሌቶች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ32 መ/ቤቶች	453 ተሽከርካሪዎችና 18 ሞተር ብስክሌቶች
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው	በ6 መ/ቤቶች	8 ተሽከርካሪዎች
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው	በ6 መ/ቤቶች	8 ተሽከርካሪዎች
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መ/ቤቶችና ድርጅቶች ስም የሆነ	በ8 መ/ቤቶች	182 ተሽከርካሪዎች
የተሽከርካሪዎችን ፋይል የማያደራጁ	በ3 መ/ቤቶች	
የሞተር ቁጥር የሌላቸው	በ2 መ/ቤቶች	8 ተሽከርካሪዎች
የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው የማይሰራ	በ5 መ/ቤቶች	17 ተሽከርካሪዎች
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት ያለባቸው	በ3 መ/ቤቶች	4 ተሽከርካሪዎች

መኖራቸው ታውቋል፡፡

85. በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው፤ የማያገለግሉት ደግሞ

በመንግሥት መመሪያ መሠረት እንዲወገዱና ሊብሬ ያልቀረበላቸው አስፈላጊው ማስረጃ ተሟልቶ እንዲወጣላቸው ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

መሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲትን በተመለከተ

86. የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS III) ፕሮጀክት ተከታታይ (Continuous) ኦዲት በየሩብ ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተልኮ ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍነው የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን ነው፡፡

87. በዚህም መሠረት ከሁሉም ክልሎች በናሙና በተመረጡ በ305 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ የክልል ሴክተር ቢሮዎች ተከታታይ ኦዲት እና አንድ ፕሮግራም አቀፍ የሆነ የማጠቃለያ ኦዲት ለማካሄድ ታቅዶ በ238 (78%) ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የፕሮግራሙ ፈጻሚ በሆኑ የሴክተር ቢሮዎች እንደዚሁም ፕሮግራም አቀፍ የሆነውን የማጠቃለያ ኦዲት በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ደረጃ ለመፈጸም ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በዕቅድ ወቅት ያልታወቀና በዕቅድ ያልተያዘ ነገር ግን ለመንግሥት ለሚደረገው የገንዘብ ፍሰት የኦዲት ሪፖርታችንን መሠረት የሚያደርገው በፍትሃዊ መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ አቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Services-ESPES, Program for Result) የገንዘብ ፍሰት አመልካቾችን የማረጋገጥ ሥራ (Verfication) በ64 ወረዳዎች በመከናወኑ አጠቃላይ ክንውኑን 302 ወረዳዎች ወይም የዕቅዱ 99.02% መፈጸም ተችሏል፡፡

የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲትን በተመለከተ

88. በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የተዘጋጀው 2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት የተጠቃለለ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተላከ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት የታዩት ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

89. በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 11 አንቀፅ 59 መሰረት ሚኒስቴሩ ከመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚደርሰውን የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርትና የማእከላዊ ግምጃ ቤትን ሂሳብ በማጠቃለል የፌዴራል መንግስትን አመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማዘጋጀት እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ ሂሳብ አቅራቢ መ/ቤቶች በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኦዲት ተደርገው በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የተስተካከለ ሂሳብ መግለጫ ሳያቀርቡ ሂሳቡ የተጠቃለለ መሆኑ ታውቋል፡፡

90. መንግስት ከውጭ ሀገር ተበድሮ በመልሶ ማበደር ስምምነት ለልማት ድርጅቶች ያበደረውን ገንዘብ ተበዳሪዎች በገቡት ውል መሠረት ወቅቱን ጠብቀው ተመላሽ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ2008 በጀት ዓመት በበጀት ከተያዘው ውስጥ እስከ ሰኔ 30/2008 ዓ.ም ድረስ ከሦስት ድርጅቶች ላይ በድምሩ ብር 184,611,464.40 የወለድ ሂሳብ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

91. በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 5 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 2ሀ መሰረት አመታዊ በጀት ሲዘጋጅ በበጀት አመቱ ውስጥ ሊሰበሰብ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ሊይዝ እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንጻር በ2008 በጀት አመት ውስጥ ከአገር ውስጥ ሊሰበሰብ የሚችለው ገቢ ሙሉ በሙሉ በበጀት የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በበጀት ሳይካተት በተለያዩ የሂሳብ አርዕስቶች ብር 400,369,539.68 ተሰብስቦ ተገኝቷል፡፡

92. ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር መንግሥት በሽያጭ ያስተላለፋቸውን ድርጅቶች እና የመንግስት ትርፍ ድርሻ ክፍያ በተያዘላቸው ዕቅድ መሰረት ገቢ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ እስከ ሰኔ 30, 2008 ዓ.ም ድረስ ከሰባት የተለያዩ ድርጅቶች በድምሩ ብር 3,554,039,809.54 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

የክዋኔ ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶችን በተመለከተ

93. መ/ቤታችን የፋይናንስና የሕጋዊነት (regularity) ኦዲቱን ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ በሂደት ትኩረቱን በክዋኔ ኦዲት ላይ ለማድረግ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በመንግሥት መ/ቤቶች የተቀረፁ ኘሮግራሞችና ኘሮጀክቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ መምታታቸውን ለማረጋገጥ የክዋኔ ኦዲት ተከናውኗል፡፡

94. በዚሁ መሠረት በየካቲት 2008 ተጀምረው እስከ ጥር 30/2009

የሚጠናቀቁ 18 የክዋኔ ኦዲቶችንና 8 የክትትል ኦዲቶችን ለማከናወን በእቅድ የተያዘ መሆኑ ይታወቃል፡፡

95. የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ አፈጻፀም ሲታይ የ18 አዳዲስ ክዋኔ ኦዲቶች ሥራ በታቀደው መሠረት ተጠናቆ ሪፖርታቸው የተላከ ሲሆን የክትትል ኦዲቱን በተመለከተ የ7 ክትትል ኦዲቶች ተጠናቆ ሪፖርቶቹ ወጪ የሆኑ ሲሆን በቀሪው 1 የክትትል ኦዲት ምትክ አንድ አዲስ የክዋኔ ኦዲት ተጠናቆ ረቂቅ ሪፖርቱ ለኦዲት ተደራጊው ተልኮ የመውጫ ስብሰባ እየተጠበቀ በመሆኑ በአጠቃላይ የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ ክንውኑ 100% ሆኗል፡፡

96. የኦዲት ሪፖርታቸው ወጪ የሆኑት የ18 ክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችና የ7ቱ የክትትል ኦዲት ሪፖርቶች ለምክር ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት የተላኩ ሲሆን ዋና ዋና ግኝቶቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የማዕቀፍ ግዥ የኮንትራት ውል አፈጻጸምን በተመለከተ

97. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በማዕቀፍ ግዥ እቃ ለማቅረብ ጨረታውን ያሸነፉትን አቅራቢዎች ከመወሰኑ እና ከአሸናፊ ድርጅቶች ጋር ውል ከመፈራረሙ በፊት የአቅራቢዎችን ቀድሞ የነበረውን የመልካም ስራ አፈፃፀም የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት የዘረጋ ቢሆንም ተግባራዊ ያላደረገ በመሆኑ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ውስጥ አንዳንድ አቅራቢ ድርጅቶች በጊዜ የማቅረብ ችግር እንዳለባቸው በተደጋጋሚ ከተለያዩ ከማዕቀፍ ግዥ ተጠቃሚ መ/ቤቶች ቅሬታ ቢቀርብም አገልግሎቱ በውሉ መሰረት ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ሲገባው ይልቁንም የማዕቀፍ ውል ስምምነቱን በድጋሚ ለ3 ዓመት (2008-2010) ከነኚሁ ድርጅቶች ጋር ያደረገ መሆኑ፤

98. አገልግሎቱ በማዕቀፍ ግዥ የሚፈለጉ ዕቃዎችን ለማቅረብ ተወዳድረው ጨረታ ካሸነፉ አቅራቢዎች ጋር የግዥ ውል ከመፈራረማቸው በፊት አሸናፊዎቹ ለማቅረብ የተወዳደሩትን እቃዎች በተፈለገው ጥራት፣ ጊዜና፣ መጠን ወዲያውኑ ለማቅረብ የሚያስችል በቂ አቅም (ክምችትን ጨምሮ) ያላቸው መሆኑን ሊያረጋግጥና አቅራቢዎቹም በውሉ መሰረት በተፈለገው ጊዜ፣ መጠንና ጥራት ሊያቀርቡ የሚገባ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት የመንግስት መ/ቤቶች ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና የግዥ ባለሙያዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በግዥ ትዕዛዝ (purchase order) የጠየቁት እቃዎች በሚፈለገው መጠንና ጊዜ እንዳልቀረበላቸው ይልቁንም ዕቃዎቹን ለማቅረብ ጨረታ

ካሸነፉት አቅራቢዎች ውስጥ አባድር ሾፒንግ ሴንተር ኃ/የተ/የ/ማ የካቲት ወረቀት ሥራዎች ድርጅት፣ ጌድ ኃ/የተ/የግ/ማ፣ አማ ወረቀት እና የወረቀት ማሸጊያ አምራች ኃ/የ/የ/ማ፣ ኤ ኤስ ኤ ትሬዲንግ እና ራዲካል ኃ/ተ/የ/ማ እቃዎችን ከ19 እስከ 240 ቀናት ሳያቀርቡ እንዳዘገዩ የገለጹ መሆኑ፤

99. አገልግሎቱ በገቡት ውል መሰረት ያልፈፀሙ አቅራቢዎችን በመለየት በውሉና በግዥ መመሪያው መሰረት እርምጃ ሊወስድ የሚገባ ቢሆንም የመንግስት መ/ቤቶች የአቅርቦት ችግር ሲገጥማቸው የአቅራቢ ለውጥ እንዲያደርጉ በደብዳቤ ከማሳወቅና ለአንድ ጊዜ በራሳቸው እንዲገዙ ከማድረግ በስተቀር በገቡት ውል መሰረት ያልፈፀሙትን አቅራቢዎች በመለየት በውሉና በግዥ መመሪያው መሰረት እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፤

የውሃ ልማት ፈንድ ማመንጨትና ብድር አስተዳደርን በተመለከተ

100. የጽ/ቤቱን የተዘዋዋሪ ፈንድ ክምችት ለማጠናከር የሚረዱ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን በማጥናት ወይም በማስጠናት ለሚመለከተው አካል አቅርቦ በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ሲገባ የተዘዋዋሪ ፈንዱን (Revoleving Fund) ክምችት ለማጠናከር የሚረዱ ልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን ያላጠና ወይም ያላስጠና መሆኑን፤

101. ጽ/ቤቱ በአዋጅ 268/1994 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሰረት የብድር አሰጣጥና አወሳሰን መመዘኛ ረቂቅ መመሪያ በሚያዝያ ወር 2001 ዓ.ም ያዘጋጀ ሲሆን ረቂቅ መመሪያው በ14/08/2001 ለቦርድ ስብሰባ ቀርቦ በቀድሞው ውሃ ሀብት ሚኒስቴር በህግ ባለሞያ እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ከተገመገመ በኃላ ለቦርዱ እንዲቀርብ በተደጋጋሚ ቢወሰንም በውሳኔው መሰረት ተስተካክሎ እንዲጽድቅ አለመደረጉ ነገር ግን ባልጸደቀው ረቂቅ መመሪያ ለተበዳሪ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋማት ጽ/ቤቱ ብድር እየሰጠ መሆኑን፤

102. የብድር ተጠቃሚ የሚሆኑ ከተሞችን ለመምረጥ የሚያስችል ግልፅ የሆነ የከተሞች መምረጫ መስፈርት መመሪያ ተዘጋጅቶ ባለመውጣቱ ፍትሃዊነት በጎደለው መልኩ አቅም ላላቸው ከተሞች ነጻ ግንባታ የሚካሄድበትና ለትናንሽ ከተሞች በብድር ፈንድ እንዲታቀፉ የሚሰራበት የተዘበራረቀ አሰራር የተፈጠረ መሆኑ፤

103. ጽ/ቤቱም ከተበዳሪዎች ለሚሰበስበው የፕሮጀክት መዋጮ (Matching

Fund) የብድሩን ምን ያህል ፐርሰንት ማዋጣት እንደሚገባቸው የሚወስን ግልጽ መስፈርት ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ሲገባ ያላዘጋጀ ከመሆኑም በላይ በዓለም ባንክ ብድር የተከናወኑ ስድስት ከተሞችን በተመለከተ ወልቂጤ በ2003፣ ቡታጅራና ሆሳዕና በ2006፣ እንዲሁም አሶሳ በ2007 ዓ.ም የተጠናቀቁ ቢሆንም ከወልቂጤ ብር 3,716,216.73 ከሆሳዕና ብር 6,923,158.15 ከቡታጅራ ብር 2,715,529.00 ከአሶሳ ብር 1,644,866.60 በጠቅላላው ብር 14,999,770.48 እስካሁን ድረስ ያልተሰበሰበ የፕሮጀክት መዋጮ ገንዘብ መኖሩ እንዲሁም ሐረር፣ ክብረመንግስትና አክሱም ምንም የፕሮጀክት መዋጮ ገንዘብ ያላዋጡ መሆናቸውና የሰበታ ከተማ ብር 5,121,713.50 እና የቡራዩ ከተማ ብር 1,861,704.00 በብልጫ እንዲከፍሉ መደረጉ፤

104. በአዋጅ 581/2000 አንቀፅ 6 መሰረት ጽ/ቤቱ ከተበዳሪዎች መሰብሰብ የሚገባውን የብድር ተመላሽና ወለድ በወቅቱ ሊሰበሰብ የሚገባ ቢሆንም ቅድሚያ አግኝተው ከተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ላይ ያልተሰበሰበ የብድር ተመላሽና ወለድ በድምሩ ብር 111,954,101.70 መሆኑ፤

የኢነርጂ ብቃት (Energy Efficiency) እና ቁጠባ(Energy Conservation) አፈጻጸም

105. በኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006 መሠረት የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ለማስፈጸም የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ (Energy Efficiency and conservation) ደንብና መመሪያዎች በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጁ ቢሆንም አለመጽደቃቸው፤

106. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢነርጂ ብቃት የመፈተሻ ስርዓት ሊያወጣና ሊተገብር፤ የኢነርጂ ብቃት መፈተሻ ላብራቶሪዎችን ሊያቋቁም የሚገባ ቢሆንም ማስፈጸሚያ ደንቡ ባለመጽደቁ ስርዓቱን ያልዘረጋ እና የኢነርጂ ብቃት መፈተሻ ላብራቶሪዎችን ያላቋቋመ መሆኑ፤

107. መ/ቤቱ በጥናት የተደገፈ የኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ ፕሮግራም በማዘጋጀት ዝርዝር የትግበራ መርሀ ግብር በመንደፍና በመተግበር የፕሮግራሙን አፈጻጸም በየጊዜው ሊገመግም እና ውጤት ማስገኘቱን ሊለካ የሚገባ ቢሆንም ለሀገር አቀፍ ፕሮግራም ዝግጅት የሚሆኑ ጥናቶችን በረቂቅ ደረጃ ከማዘጋጀት ውጭ አነኚህ ተግባራት አለመከናወናቸው፤

108. ባለስልጣኑ የኢነርጂ ብቃት ደረጃዎች ኮድ፣ የኢነርጂ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ኮድ እንዲሁም የኢነርጂ ኦዲት ኮድ ሊያወጣና አፈፃፀሙንም ሊከታተል የሚገባ ቢሆንም የተለያዩ መመሪያዎች እና ኮዶች በረቂቅ ደረጃ እንደተዘጋጁ ሆኖም ግን የኢነርጂ ደንቡ ባለመጽደቁ ተግባራዊ ለማድረግ እንዳልተቻለ እንዲሁም የኢነርጂ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ኮድ ገና እየተሰራ መሆኑ፤

109. ባለስልጣኑ በብሄራዊ ደረጃ ከከፍተኛ ኢነርጂ ተጠቃሚዎች ጋር የኢነርጂ ብቃትን የሚያበረታታ የፈቃደኝነት ስምምነት በመግባት የኢነርጂ ብቃትን የሚያበረታታ የተሻለ የኢነርጂ አጠቃቀም ያላቸው ተቋማት የፈቃደኝነት እንዲሁም ኃይል አባካኝ ወይም የኃይል ብክነት የሚታይባቸው ተቋማት ጋር ደግሞ አስገዳጅ ስምምነቶችን የማያደርግ መሆኑን፤

110. የሀገሪቱ የኢነርጂ ፍላጎት፣ የተመረተ፣ ጥቅም ላይ የዋለ እና ያልዋለ የኢነርጂ መጠን በባለስልጣን መ/ቤቱ ሊታወቅ የሚገባ ቢሆንም ጥቅም ላይ የዋለ እና ያልዋለ የኢነርጂ መጠን በባለሥልጣኑ የማይታወቅ መሆኑ፤

111. ኢነርጂ ቆጣቢ የሆኑ የኢነርጂ መጠቀሚያ ቴክኖሎጂዎች ለገበያ ከመቅረባቸው በፊት የሚያሟሉት ደረጃ ሊታወቅ፤ በየመሳሪያዎቹና ዕቃዎቹ ላይ ደረጃቸውን የሚገልጽ ግልጽ የተለጣፊ ምልክት ተዘጋጅቶ ሊለጠፍና የተለጣፊ ምልክቱንም ለአቅራቢዎቹ የመጠቀም መብት የሚያረጋግጥ ፈቃድ ሊሰጥ የሚገባ ቢሆንም እነኚህ ተግባራት ያልተፈጸሙ መሆኑ፤

112. በአዋጅ ቁጥር 810/2006 አንቀጽ 23 መሰረት የኢነርጂ ፈንድ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ ዘርፍ ለሚሳተፉ የኢነርጂ ተጠቃሚ ተቋማት የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም አለመፈጸሙ፤

113. በአዋጅ ቁጥር 810/2006 አንቀጽ 19 መሰረት ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ አመራር የስራ ክፍል (Energy Management Unit) ሊያቋቁሙ የሚገባ ቢሆንም ድርጅቶቹ አስፈላጊነቱ ላይ ግንዛቤ ስለሌላቸውና ባለሥልጣኑም ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ባለመሥራቱ በድርጅቶቹ ውስጥ የኢነርጂ አመራር የስራ ክፍል (Energy Management Unit) ያልተቋቋመ መሆኑ፤

የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ እና የውሃ ሀብት አስተዳደር አፈጻጸም

114. ባለሥልጣኑ በሶስት ንዑስ ተፋሰሶች (ሀዋሳ፣ ዝዋይ ሻላ እና አባያ ጫሞ) ላይ ንዑስ ተፋሰሶቹ ያሉበትን ሁኔታ ለመረዳት የዳሰሳ ጥናቶችን ያደረገ ቢሆንም በጥናቱ መሰረት የተለያዩ ጉዳት አይነትና መጠን ያላቸውና ከሐይቆች ወይም ከውሃ አካላት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው አካባቢዎችን ለማልማትና ለመንከባከብ ቅድሚያ ለመስጠት የሚያስችል ግልጽ የሆነ መምረጫ መስፈርት ያልተዘጋጀ መሆኑ፤

115. ባለስልጣን መ/ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ በሀይቆችና ወንዞች ላይ በተለያዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች የሚደርሱትን ተጽዕኖዎች ለመቀነስና ለመከላከል ከውሃ ሀብት ልማትና እንክብካቤ ጋር ተያይዞ የሚከናወኑ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን ለመምራት እና ለማስተዳደር የሚረዳ መመሪያ ወይም የትግበራ ማንዋል ያላዘጋጀ መሆኑ፤

116. በሐይቆቹ ተፋሰስ ውስጥ የሚሰሩ የልማትና የእንክብካቤ ስራዎች ደረጃቸውን የጠበቁና ዘላቂነታቸው በተረጋገጠ መልኩ ሊከናወኑ የሚገባ ቢሆንም በተፋሰሱ ውስጥ በባለስልጣኑ ድጋፍ የተሰሩ የስነ አካላዊ (physical structures) እና የስነ ህይወታዊ (biological conservation) ስራዎች በቅንጅት እንዲደጋገፉ አለመደረጉ፤ ክትትል የማይደረግላቸውና ከፊሎቹ አገልግሎት መስጠት እንደጀመሩ የፈረሱ መሆኑን፣ የክትር (ጋቢዮዎን) ስራዎች የጎርፍ ግፊት መጠን /discharge rate/ ሳይጠና የተሰሩ አካላዊ ስራዎች ርቀታቸውን /interval/ ጠብቀው አለመሰራታቸውን፤ በተሰራው ጋቢዮዎን አልፎ የሚፈስ ውሃ የሚያርፍበት ቦታ /Apron/ ያልተሰራ በመሆኑ ተጨማሪ የመሬት መቦርቦር እያስከተለ መሆኑን፣ እንዲሁም በየጊዜው የችግኝ ተከላ በተፋሰሶቹ ውስጥ የሚከናወን ቢሆንም በአብዛኛው የማይጸድቁ (low survival rate) መሆኑን ለምሳሌ በወረዳዎች የችግኞች ተከላ ውጤታማ ነው እየተባለ በሪፖርት የሚገለጸው በአካል ሲታይ ችግኞቹ የጸደቁ አለመሆናቸው መታየቱ እና በአርሶ አደሩ ተሳትፎ በተፋሰሱ ውስጥ የሚከናወኑ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች በየዓመቱ የሚታረሱና የሚበላሹበት ሁኔታ መኖሩን፤

117. ከከተሞችና ኢንዱስትሪዎች የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎች ወደ ወንዞች ከመለቀቃቸው በፊት ከባለሥልጠኑ አክሞ ለመልቀቅ ፈቃድ ማግኘት ያለባቸው ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በሀዋሳ ንዑስ ተፋሰስ ውስጥ ከቢ.ጂ.አይ (BGI) ኢትዮጵያ ፒ.ኤል.ሲ

(ሀዋሳ ቢራ ፋብሪካ)፣ ኢታብ ሳሙና ፋብሪካ፣ ታቦር ሴራሚክ ፋብሪካ፣ ሞሃ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ፣ እና ከሃዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ከምርት ክፍሎች የሚወጣው ብክለት ያለው ፍሳሽ በጨፌ ረግረጋማ መሬት አማካኝነት በጥቁር ውሃ ወንዝ በኩል ወደ ሀዋሳ ሀይቅ የሚገባ መሆኑ እንዲሁም በዝዋይ ሻላ ንዑስ ተፋሰስ ውስጥ በናሙና የታዩ በዝዋይ ከተማ ከመስኖ እርሻ ማሳ እና ከአበባ ልማት ድርጅቶች ሼር ኢትዮጵያና በሼር ኢትዮጵያ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሚገኙ Herburg Roses Plc, AQ Roses, Zway Roses የሚወጣ ፍሳሽ ኬሚካል ቆሻሻ ሳይታከም ቀጥታ ወደ ዝዋይ ሀይቅ የሚገባ መሆኑን፤

118. በሀይቆችና በውሃ አካላት አካባቢ የሚካሄዱ ማናቸውም የልማት ፕሮጀክቶች በሚያስጠኗቸው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናቶች ላይ ባለስልጣን መ/ቤቱ የውሃ አካላቱ ደህንነት በዘላቂነት የተጠበቀ መሆኑን የሚያረጋግጡ ሆነው መጠናታቸውን እንዲያረጋግጥ ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት አስተያየት እንዲሰጥ የማይደረግ መሆኑ፤

119. የኢትዮጵያ ውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 197/1992 ተቆጣጣሪው አካል አግባብ ካለው የመንግስት አካል ጋር በመመካከር እና በመተባበር የተወሰኑ የውሃ አካላት ዳርቻዎችን ወሰን መከለል እና በተከለሉ የውሃ አካላት ዳርቻዎች ክልል ውስጥ ያሉ የእጽዋት ሽፋኖች ወይም ዛፎች እንዳይመነጠሩ ወይም እንዳይቆረጡ እንዲሁም የመኖሪያ ቤቶች እንዳይገነቡ መከልከል እንደሚቻል ቢገልጽም በተፋሰሱ የረግረጋማ መሬት አስተዳደርና የሀይቆች ዳርቻ ክልልን የሚመለከት ጥናት ያልተካሄደ እና የሀይቆች ዳርቻ ክልል (Buffer Zone) እና የረግረጋማ መሬት ወሰን የሚያሳይ ካርታ ያልተዘጋጀ መሆኑን፤

120. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተፋሰሱ ውስጥ ለተለያዩ ሥራዎች ውሃን ለሚጠቀሙ የአጠቃቀም ፈቃድ ሊሰጥና በየዓመቱ ፈቃዱን ሊያድስ ሲገባ በባለሥልጣኑ መረጃ መሠረት በተፋሰሱ ውስጥ ውሃን ለተለያዩ የልማት ሥራዎች የሚጠቀሙ 319 የውሃ ተጠቃሚዎች ውስጥ የውሃ አጠቃቀም ፈቃድ የሰጠው ለ14 ተጠቃሚዎች ብቻ መሆኑና ይህ ኦዲት እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ፈቃድ ለማውጣት በሂደት ላይ ያሉት 5 ብቻ መሆናቸውና የተቀሩት 300 (94%) የውሃ ተጠቃሚዎች የውሃ ፈቃድ ሳይወስዱ ውሃን የሚጠቀሙ መሆኑ፤ በተጨማሪም ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአጠቃላይ በተፋሰሱ ውስጥ የሚገኙ የውሃ ተጠቃሚዎች (የመስኖ፣ ፋብሪካዎች፣ ሪዞርቶች...) ብዛት እና የሚጠቀሙትን የውሃ መጠን ለይቶ የማያውቅና የአከፋፈል ታሪፍ መመሪያም ያልተዘጋጀ ከመሆኑም ሌላ በተፋሰሱ ላይ ለተለያየ ሥራ የተተከሉ የውሃ መሳቢያ

ፓምፖች ብዛታቸው እና አቅማቸው ምን ያህል እንደሆነ መረጃ የሌለው መሆኑን፤

የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ አፈጻጸምን በተመለከተ

121. በአገሪቱ ውስጥ የሚከናወኑ የእንስሳት የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች የሚመሩበት እና ሊደረስበት የታሰበውን አቅጣጫ የሚያመላክት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በእንስሳት እና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴርም ሆነ በናሙና ተመርጠው በታዩ የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት፣ የክልል (የኦሮሚያና ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች)፤ ዘንና ወረዳ እንስሳትና ዓሳ ሀብት ጽ/ቤቶች ተቀርጾና ፀድቆ በስራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ፤

122. አገር አቀፍ የእንስሳት የርቢ፣ የመረጣ፣ የብዜት፣ የአጠቃቀምና የጥበቃ ፕሮግራም የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዝርያ ማሻሻያ ሥራን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት (የእንስሳትና ዓሳ ኃብት ሚ/ር ሥር የሚገኙ የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት፣ የፌዴራልና የክልል ግብርና ምርምር ማዕከላት፣ የብሔራዊ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ቁጥጥር ባለሥልጣን፣ ሌሎች የግልና የመንግሥት እንስሳት እርባታ ማዕከላት) ጋር በመቀናጀት ፕሮግራሙ የማያዘጋጅ መሆኑ፤

123. ለዝርያ ማሻሻል የሚመረጡ እንስሳት ጤና አገልግሎትን ለማሻሻል፣ የስጋት ትንተና ለማካሄድና መጠኑን ለመለየት፣ በሽታን ለመከላከልና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሥርዓት የተዘረጋ ቢሆንም የሰበታ የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ በሪፖርት ቁ.322/16 እ.ኤ.አ በ16/09/16 በተጻፈ ደብዳቤ በሆለታ አስኳል የእናቶች መንጋ ማዕከል በሚገኙ 220 እንስሳት ላይ ምርመራ አድርጎ ሁሉም በመተንፈሻ አካል በሽታ (IBR) የተጠቁ መሆናቸውን ያረጋገጠና በመተንፈሻ አካል (IBR) በሽታ የተጠቁ እንስሳቶች በዘር (genetic) አማካኝነት በሽታን እንደሚያስተላልፉ ቢያሳውቅም ችግራቸው እየታወቀ ከነዚህ ላሞች የተወለደ ኮርማ ለዝርያ ማሻሻያ ሥራ ከሆለታ አስኳል መንጋ ማዕከል ተመርጦ በቃሊቲ ዝርያ ማሻሻያ ማዕከል ዘሩ ለተጠቃሚው እንዲሰራጭ መደረጉ፤

124. ነባር እና አዳዲስ የእንስሳት ዝርያዎችና ዘሮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በልዩ እንክብካቤ፣ ጥብቅ ስፍራዎች ተይዘው እንዲራቡ እንዲጠበቁና ጥቅም እንዲሰጡ ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም መ/ቤቱ በወተት

ዳልጋ ከብት ላይ ብቻ የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎችን የሚያከናውን በመሆኑ የሀገር ውስጥ ዝርያ የሆኑት የሸኮና አቢጋር ዝርያዎች እየተባዙ ባለመሆናቸው ዝርያዎቹ ወደ መጥፋት ደረጃ እየተቃረቡ መሆኑ፣ እንዲሁም በዳልጋ ከብት ላይ በሀገር ውስጥ የቦረና፣ የበጋይት፣ የፎገራ፣ የሆሮ፣ የሸኮና አቢጋር ዝርያዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ የተለዩ ቢሆንም እነዚህን ዝርያዎች በመጠበቅና በማባዛት ማሰራጨት አለመቻሉ እንደዚሁም ከነዚህ ዳልጋ ከብቶች ውጪ በሌሎች የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኙ በሚችሉ የፍየል፣ የበግ፣ የሥጋ ዳልጋ ከብት፣ ፈረስ ወ.ዘ.ተ. ላይ የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎች እንዲከናወኑ አለመደረጉ፤

የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለሥራ ተቋራጮች ለሚሰጠው ፈቃድና ቁጥጥር ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን በተመለከተ

125. ለሁሉም አይነት ሥራ ተቋራጮች (ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ፣ የህንፃ ሥራ ተቋራጭ፣ የመንገድ ሥራ ተቋራጭ እና ልዩ ሥራ ተቋራጭ) የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ በየደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት (የመሳሪያ፣ የተሽከርካሪና የሰው ኃይል) ያሟሉ መሆኑ የሚያረጋግጥበት፣ በእድሳት ወቅትም በሰነድና በአካል መኖራቸው የሚረጋግጥበት የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመውሰድ የመጡ ስራ ተቋራጮች የሚያቀርቧቸው እና መሟላት ያለባቸውን መሳሪያዎችና ተሽከርካሪዎች በሰነድ መኖራቸውን የሚያረጋግጥ ቢሆንም በአካል መኖራቸውን በተመለከተ ግን ፈቃድ ሲሰጥም ሆነ ሲታደስ የማያረጋግጥ መሆኑ፤

126. ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ፈቃድ ያሳደሱ መሆናቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር፣ ያላሳደሱትን በተቋራጭነት ሥራ ላይ እንዳይሰማሩ ለማድረግ ህብረተሰቡ፣ የግል ድርጅቶች፣ የመንግስት ተቋማት እና የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ ያለበት ቢሆንም በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየዓመቱ ፈቃዳቸውን ማሳደሳቸውን የማይከታተልና የማይቆጣጠር በመሆኑ እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ ፈቃድ ከወሰዱት ከ11,912 ስራ ተቋራጮች ውስጥ 5,321 ስራ ተቋራጮች ፈቃድ ያላሳደሱ ሲሆን ህብረተሰቡ፣ የግል ድርጅቶች፣ የመንግስት ተቋማት እና የሚመለከታቸው ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት እንዲያውቁት ያላደረገ መሆኑ፤

የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ዕቅድ አፈፃፀም፣ የግንባታ እና ሌሎች ግብዓቶች ለማሟላት የታቀደው ዕቅድ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ስኬታማ መሆኑን በተመለከተ

127. የኘሮጀክቱን አጠቃላይ የግንባታ አፈፃፀም ሂደት (ግንባታዎቹ በምዕራፍ ተከፋፍለው መቼ እንደሚሰሩ፣ ለእያንዳንዱ ሥራ ምን ያህል ወጪ እንደሚጠይቅ፣ ፕሮጀክት ፅ/ቤቶች የት እንደሚቋቋሙ፣ ለካሳ ክፍያ የተያዘው ወጪ፣ ለቅድመ ግንባታ ሥራዎች የሚያስፈልጉ ዝግጅቶችና ወጪዎች፣ ባለድርሻ አካላት ሚናቸው መለየቱን...) የሚያሳየው መሪ ዕቅድ (Master Plan) የተዘጋጀ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲዎቹ ሥራቸውን ለመጀመር የሚያስፈልጉ ግብዓት ሆነ የላቦራቶሪ የመጽሐፍት ግዥ በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑ፤

128. የአስራ አንድ ዩኒቨርስቲዎች የግንባታ ኘሮጀክት ዕቅድ ለመተግበር የሚያስችል በወር፣ በሩብ ዓመት፣ በግማሽ ዓመት እንዲሁም በዓመት ተከፋፍሎ የዕቅድ ትግበራ መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ ሊተገበር በሚችል መልክ ተከፋፍሎ ሊቀመጥ ሲገባ ካለመቀመጡም በላይ የ11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት በየካቲት 30/2009 ዓ.ም የመጀመሪያው የግንባታ ምዕራፍ መጠናቀቅ ያለበት ቢሆንም እስከ የካቲት 25/2009 ዓ.ም ድረስ የተደረገው ግምገማና ያሉበትን ደረጃ ከ38 ከመቶ (ቀብሪደሃር ዩኒቨርሲቲ) እስከ 78 ከመቶ (የጂንካ ዩኒቨርሲቲ) ድረስ ሲሆን የኦዳቡልቱም ዩኒቨርሲቲ ግንባታው ጭራሹኑ አለመጀመሩ፤

በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የወረዳ ኔት አፈፃፀም

129. የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም መመሪያው በረቂቅ ደረጃ ከመዘጋጀቱ በስተቀር በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ አለመሆኑ፤

130. የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት አላግባብ ክፍያ እንዳይከፍሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት አላግባብ ክፍያ ለኢትዮ ቴሌኮም እየፈጸሙ መሆኑ፤

131. የወረዳኔት አገልግሎት ለመዘርጋት የወጣው ወጪ ምን ያህል እንደሆነ በትክክል ተመዝግቦ ሊያዝ፤ ዝርጋታቸው የተጠናቀቀ የቪድዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት ደግሞ የተሟላ አገልግሎት ሊሰጡ ይህ አገልግሎት በመሰጠቱ

የተገኘው ፋይዳ ሊጠና እና ውጤቱም ተመዝግቦ ሊያዝ የሚገባ ቢሆንም ለወረዳኔት አገልግሎት ለመዘርጋት የወጣው ወጪ በትክክል ምን ያህል እንደሆነ በሚኒስቴር መ/ቤቱም ተመዝግቦ ያልተቀመጠና የማይታወቅ ከመሆኑም ሌላ በርካታ የቪዲዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት ዝርጋታቸው ተጠናቀው አገልግሎት ሳይሰጡ ለበርካታ ዓመታት የተቀመጡ በየክልሉ መኖራቸው፤

ለአካል ጉዳተኞች የሚደረገው ድጋፍና ክትትልን በተመለከተ

132. ሀገሪቱ የፈረመችውን የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንንሽን ለማስፈፀም በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚመራ የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት፣ በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ የሚሠሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት ተቋማት እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትን ያካተተ ብሔራዊ የአተገባበርና የክትትል አስተባባሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ በ2004 ዓ.ም ብሄራዊ የድርጊት መርሃ ግብር በማፅደቅ በሚመለከታቸው ጉዳይ መሰረት ለመፈፀም የተለያዩ አካላት ኃላፊነት የወሰዱ ቢሆንም የኮሚቴው አባላት በተደራጀ ሁኔታ በዓመታዊ ዕቅዳቸው አካትተው ስለማቀዳቸው እንዲሁም በዕቅዱ መሰረት ስለመተግበራቸውና የዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲያቀርቡ በማድረግ በቅንጅት ኃላፊነታቸውን ስለመወጣታቸው የክትትልና ድጋፍ ስራ በአግባቡ እየተከናወነ ካለመሆኑም በላይ ይህን የማይፈፅሙ ተቋሚት የሚጠየቁበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤

133. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬሽንን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ አካል ጉዳተኞች በኮንቬንሽኑ የተቀመጡ መብቶቻቸውን ለመጠቀም እንዲችሉ ለማድረግና በማህበራዊ ዘርፍ ለተቀመጡ መብቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ዝርዝር የአፈፃፀም ማንዋል (ሜይኒስትሪሚንግ ጋይድ ላይን) ካለመውጣቱም ሌላ የሚመለከታቸው አካላትም በኃላፊነታቸው መሰረት ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ እንዲያወጡ ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፤

134. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካል ጉዳተኞች ላይ መድሎ/አድሎ የሚያስከትሉ በስራ ላይ ያሉ ሕግጋትን፣ ደንቦችንና መብትን የሚነኩ የቆዩ ልማዶችንና አሰራሮችን ለማሻሻል ወይም ለማስወገድ አዲስ ህግ እንዲወጣ ማስደረግን ጨምሮ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ለመውሰድ በሚያስችለው መልኩ ነቅሶ በማውጣት የሚመለከታቸው አካላትን እና አካል ጉዳተኞች ማህበራትን አወያይቶ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ እርምጃ እንዲወሰድባቸው የሚያስችሉ ሥራዎችን አለመስራቱ፤

በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የጉምሩክ ስነ ሥርዓት አፈጻጸም

135. ባለስልጣኑ የጉምሩክ ትራንዚት ስነ-ሥርዓት በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ እና በስጋት ስራ አመራር አሰራር ስርዓት መሰረት ለመምራት የኤሌክትሮኒክስ የጭነት መቆጣጠሪያ ስርዓት (Electronics Cargo Tracking and Monitoring System) ለመዘርጋት ከሀይ.ጅ.ቴክ ካምፓኒ ጋር ጥር 7/2003 ዓ.ም በ2,500,000.00 የአሜሪካን ዶላር የውል ዋጋ እና ከውሉ ሁለተኛ አመት ጀምሮ እስከ አምስተኛው ዓመት በየአመቱ ለስራ ማስኬጃ ወጪዎች በሚከፈል 289,000 የአሜሪካን ዶላር ውል ተፈራርሞ በቀጣዮቹ አምስት አመታት ጊዜ ውስጥ በትንሹ 10,000 ተሽከርካሪዎችን ወደ ስርአቱ በማስገባት ወደ ሙሉ ትግበራ እንደሚገባ የውል ስምምነቱ ቢገልጽም እስከ 2008 በጀት አመት መጨረሻ 312 (3%) ተሽከርካሪዎች ብቻ የካርጎ ትራኪንግ መሳሪያ የተገጠመላቸው መሆኑ እና የተዘረጋው የካርጎ ትራኪንግ ሲስተም ከኢትዮጵያ መግቢያ በር ጋላፊ ጀምሮ ሲሆን ከጅቡቲ ወደብ እስከ ጋላፊ ባለው ስፍራ በውሉ መሰረት ስርአቱ ያልተዘረጋ መሆኑን፤

136. በባለስልጣኑ በስምንት የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች በዘመናዊ የፍተሻ መሳሪያ (Scanning Machine) የታገዘ አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ በ2003 ዓ.ም ወደ ስራ የተገባ ቢሆንም ከስምንቱ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ውስጥ በጋላፊ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብቻ አገልግሎቱ እየተሰጠ ሲሆን በቀሪዎቹ ሰባት ጣቢያዎች አገልግሎቱ ያልተጀመረ መሆኑ፤

137. በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት አየር በአየር በ190 የማስጫኛ ሰነድ ለወጡ እቃዎች የኢትዮጵያ አየር መንገድ እቃዎችን ለማን እና መቼ እንዳስረከባቸው ዝርዝር መረጃ የተጠየቀ ቢሆንም አየር መንገዱ በ83 የማስጫኛ ሰነዶች ለመጡ እቃዎች ብቻ የእቃዎቹ ባለቤት ናቸው የተባሉትን ማረጋገጫ የሰጠ ሲሆን በ107 የማስጫኛ ሰነድ ለወጡ ዕቃዎች ማረጋገጫ አለማቅረቡና ከመጋዘን አየር በአየር ለወጡ ዕቃዎች በግምታዊ ዋጋ ብር 101,932,491 ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ የተጠየቀ መሆኑ፤

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማነትን በተመለከተ

138. አገልግሎቱ አዳዲስ ኃይል ፈላጊ ደንበኞችን መዝግቦ ሊይዝና በከፈሉበት ቀን ቅደም ተከተል መሰረት ማስተናገድ እንዳለበት በሪቴል ቢዝነስ የደንበኞች ፓሊሲና ፕሮሲጀር ላይ የተገለፀ ቢሆንም የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት በዚህ መሰረት እየተገበሩ ስለመሆኑ ለማጣራት በናሙና ከታዩት 6 ሪጅኖች እና 15 አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ከምዕራብ አዲስ አበባ ሪጅን በስተቀር በተቀሩት አምስት ሪጅኖች እና በ15ቱም አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ደንበኞችን ያለቅደም ተከተላቸው የሚስተናግዱ መሆኑ፤

139. በሪጅኖች እና ዲስትሪክቶች ስር ያሉትን የደንበኞች ዝርዝር መረጃ በአግባቡ የተያዙ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ተመርጠው በታዩት 15 አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ከምስራቅ ሪጅን ሀረር የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ቁጥር 1 እና ከገላን የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል በስተቀር ሌሎቹ 13 ማዕከላት ያለው የደንበኞች መረጃ አያያዝ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት በሚያመች ሁኔታ የተደራጀ ካለመሆኑ በላይ በሰሜን አዲስ አበባ ሪጅን የኢንዱስትሪ ደንበኞች በውል ቁጥር 3319692፣ 3303664፣ 3308731፣ 3105629፣ 3494746፣ እና 3555651 የሚገኙ መረጃ በሚገባ ባለመያዙ ምክንያት አገልግሎቱ የደንበኞቹ አድራሻ የት እንደሆነ የማያውቅ መሆኑ፤

140. አገልግሎቱ ለመካከለኛ (ከ1,000 በላይ እስከ 60,000 የሆነ የቮልቴጅ መጠን) እና ከፍተኛ (ከ60,000 በላይ የሆነ የቮልቴጅ መጠን) የኃይል ተጠቃሚ ደንበኞች እንደ ቅደም ተከተላቸው በ45 እና በ60 ቀናት ውስጥ የቆጣሪ ማስገባት አገልግሎት ሊሰጥ የሚገባ ቢሆንም በናሙና ተመርጠው በታዩት 6 ሪጅኖች በፖሊሲና በፕሮሲጀሩ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ሳይሆን ደንበኞች አገልግሎቱን ለማግኘት ከአመታት በላይ የሚፈጅባቸው መሆኑን፤

141. በቆጣሪ ንባብ የተሰማሩ ባለሙያዎች የሚሰሩበት የስራ መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ በአፈፃፀሙም ላይ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ የሚገባ ቢሆንም በኦዲቱ በናሙና በታዩት በ15 የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከላት በቆጣሪ ንባብ የተሰማሩ ባለሙያዎች የሚሰሩበት የስራ መመሪያ የሌላቸው እንዲሁም የንባብ ባለሙያዎቹን በተጠናከረ መልኩ ለመቆጣጠርና ለመከታተል የተዘረጋ ስርዓት የሌለ መሆኑን፤

142. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ለደንበኞች የሰጠውን አገልግሎት ክፍያ በወቅቱ ሊሰበስብ የሚገባ ቢሆንም ከተለያዩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማትና ግለሰብ ደንበኞቹ ከ10 ዓመታት በፊት ጀምሮ ክፍያ ሳይፈጸምባቸው በየበጀት ዓመታቱ ተንከባሎ የመጣ ብር 132,352,369.89 ያልሰበሰበ መሆኑ፤

143. የድርጅቱ ፖሊሲና ፕሮሲጀር ላይ የአገልግሎት ክፍያን በወቅቱ የማይፈፅሙ ደንበኞች በቅድሚያ አስፈላጊው ማስጠንቀቂያ እንዲደርሳቸው ከተደረገ በኂላ ደንበኞቹ በማስጠንቀቂያው መሰረት ክፍያቸውን የማይፈጽሙ ከሆነ የኃይል ማቋረጥ ተግባር በማከናወን በህግ አግባብ የሚፈለግባቸውን ክፍያ እንዲፈፅሙ እንደሚደረግ የተገለፀ ቢሆንም በ15 ሪጅኖች ውስጥ 97 የሚሆኑ የተለያዩ የአገልግሎቱ ደንበኞች ማለትም ተቋማት፣ ድርጅቶች፣ ኤምባሲዎች እና ግለሰቦች ከ1999-2008 በጀት ዓመት ለተጠቀሙበት የኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያ ብር 80,927,531.81 ለመፈጸም ፍቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው በተቋሙ ምንም አይነት እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፤

144. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የማከፋፈያ መስመሮች እና ትራንስፎርመሮች የአገልግሎት ዘመናቸው ተጠብቆ የማሻሻያ ስራዎች እንዲሰራላቸው ሊያደርግ የሚገባ ቢሆንም በ15 ሪጅኖች ያሉት የማከፋፈያ መስመሮችና ትራንስፎርመሮች የአገልግሎት ዘመናቸውን ጠብቆ በእቅድ ላይ የተመሰረተ የማሻሻያ ስራዎች ባለመሠራቱና በአገልግሎቱ ስር ካሉት ትራንስፎርመሮች ውስጥ 40% ያህሉ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች (አሬስተር እና ድሮፕ አውት ፊውዝ) የሌላቸው በመሆኑ ምክንያት በ2007 በጀት አመት 1,029 ትራንስፎርመሮች በጭነት ምክንያት የተቃጠሉ መሆኑ፤

145. የአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል ደንበኞች ኃይል መቋረጥን ካመለከቱበት ጊዜ አንስቶ በ4 ሰዓት ጊዜ ውስጥ አገልግሎቱን ማግኘት እንዳለባቸው በደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ሰነድ ላይ የተገለፀ ቢሆንም በናሙና ተመርጠው ከታዩ 29 የድርጅቱ ከፍተኛ የኃይል ተጠቃሚ ደንበኞች (ማለትም 6 በሆቴል አገልግሎት የተሰማሩ፤ 8 ባንኮች፤ 4 የምግብ ማምረቻ ፋብሪካዎች፤ 3 የብረታ ብረት ማምረቻ ፋብሪካዎች እና 1 የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ) የአስቸኳይ ጊዜ ጥገና ክፍል ኃይል በሚቋረጥበት ወቅት በስታንዳርዱ መሰረት ምላሽ እንደማይሰጧቸውና ምርት በመበላሸቱ ለኪሣራና ተጨማሪ ወጪ እየተዳረጉ መሆኑ፤

የእንስሳት መድኀኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አፈፃፀምን በተመለከተ

146. ባለስልጣኑ ብሄራዊ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝርን ሊያዘጋጅ፣ መድኃኒቶችንና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን በየዓይነታቸው ሊመድብ፣ መዘርዝሩንም በየጊዜው ሊከልስ የሚገባ ቢሆንም ባለስልጣኑ ብሄራዊ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር መዘርዝርን ያላዘጋጀና መድኃኒቶችንና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችን በየዓይነታቸው ያልመደበ መሆኑ፤

147. በሀገር ውስጥ የተመረተም ሆነ ከውጭ ሀገር የገባ ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት በወቅቱ ደህንነቱ፣ ፈዋሽነቱና ጥራቱ ተገምግሞ ወይም ተረጋግጦ ከተመዘገበ በኋላ ጥቅም ላይ እንዲውል ሊያደርግ ሲገባ ባለስልጣኑ ከውጭ ሀገር መድኃኒት ለሚያስገቡ ለ21 የእንስሳት መድኃኒት አስመጪ ድርጅቶች ደህንነቱ፣ ፈዋሽነቱና ጥራቱ በላብራቶሪ ሳይገመገምና ሳይረጋገጥ ለ280 ዓይነት መድኃኒቶች ጊዜያዊ ፈቃድ በመስጠት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረጉና ልምዱ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የቀጠለ መሆኑ፤

148. ባለስልጣኑ የእንስሳት መኖ፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ብክለትንና ብልሽትን በሚከላከል አሰራር መሰረት መመረቱን፤ መከማቸቱንና መጓጓዙን በተሟላ መልኩ እየተቆጣጠረ የማይገኝ መሆኑ፤

የማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታ በተገባው ውል መሰረት መከናወኑን በተመለከተ፣

149. የያዩ ዩሪያ ማዳበሪያ ፋብሪካን የአዋጭነት ጥናት መንግስት በ1999 ዓ.ም ቻይና ኮምፕላንት በተባለ የውጭ ድርጅት አስጠንቶ በጥናቱም መሰረት ፋብሪካውን ለመገንባት አራት ዓመት ጊዜ የሚፈጅ መሆኑን አጥኚ ድርጅት አስቀምጦ የነበረ ቢሆንም የብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ጥናቱን በመከለስ የፋብሪካውን ግንባታ በሁለት ዓመታት ለማጠናቀቅ ሀሳብ ሲያቀርብ ሁለቱ ጥናቶች እንዲጣጣሙ ሣይደረግና በእርግጥም ይህ የሚቻል መሆኑ ሣይረጋገጥ ኮርፖሬሽኑ ግንባታውን በ2004 ዓ.ም ጀምሮ በ2006 ዓ.ም ለመጨረስ በ2004 ዓ.ም ውል የፈጸመ ሲሆን ፋብሪካው በውሉ መሰረት ሊጠናቀቅ ያለመቻሉ፤

150. እ.ኤ.አ እስከ ሰኔ 21 ቀን 2016 ድረስ ከአጠቃላይ የፕሮጀክቱ የውል ዋጋ ብር 11,084,850,000.00 ውስጥ ብር 5,653,273,500.00 ወይም የውሉ 60% ለሥራ ተቋራጩ የተከፈለ ቢሆንም እስከ መጋቢት 2009 ዓ.ም ድረስ በሶስቱ ዩኒቶች ማለትም የዩሪያ የማዳበሪያ ዩኒት 28.05%፣ የተርማል ፓዎር ፕላንት 11% እና የድንጋይ ከሰል 3.05% አጠቃላይ አፈጻጸም 42.31% ላይ የሚገኝ ሲሆን አፈጻጸሙ ዝቅተኛና በዕቅዱ መሰረት ያልተከናወነ ከመሆኑም በላይ ፕሮጀክቱ በተያዘለት ጊዜ ባለመጠናቀቁ ኮርፖሬሽኑ ከባንክ ለተበደረው ብድር ወለድ እስከ የካቲት 2008 ዓ.ም ድረስ ብቻ ብር 1,826,513,172.20 የተከፈለ መሆኑና ፕሮጀክቱ በተራዘመ ቁጥር ምንም ገቢ ሳይመነጭ ለባንክ የሚከፈለው ወለድ በከፍተኛ መጠን ሊያድግና በፋብሪካው ዘላቂነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል መሆኑ፤

151. የስራ ተቋራጩ ለእያንዳንዱ የፕሮጀክት ስራ የተተነተነ ዝርዝር የትግበራ መርሃ ግብር በወቅቱ እያወጣ ሊያቀርብና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ የስራ ተቋራጩ ለሚያከናውነው ለእያንዳንዱ የፕሮጀክት ስራ የተተነተነ ዝርዝር ዕቅድ፣ የስራ ዓይነቶችን (activities)፤ እያንዳንዱን የስራ ዓይነት ከጠቅላላ የፕሮጀክት ስራ የሚይዘው ክብደት፤ የስራዎቹ የገንዘብ መጠን፤ ስራዎቹ የሚሰሩበት ጊዜ እና የስራዎቹ ጊዜ አፈጻጸም በመከፋፈል በጊዜ መርሃ ግብሩ መሰረት በሚፈለገው ደረጃ አጠቃሎ የማያቀርብ መሆኑ፤

152. የማሽነሪዎች ዝግጅት በአገር ውስጥ በሚገኙት የሥራ ተቋራጩ እህት ኩባንያዎችና ኢንዱስትሪዎች አማካኝነት እየተዘጋጀ የሚገኝ ቢሆንም የሥራው አፈፃፀም ከፕሮጀክቱ አጠቃላይ ክንውን ጋር የማይጣጣምና የዘገየ መሆኑ፤

153. እንዲሁም የፕሮጀክቱ ወሳኝ ዕቃዎችና የግዢ የማምረትና የማቅረብ ስራ በጣም የዘገየና በታቀደለት ጊዜ እየተከናወነ አለመሆኑ፤ በግንባታ ቅደም ተከተል መሰረት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ተለይተው ያልቀረቡ መሆኑ፤ ከዕቃዎች ምርት ጋር በተያያዘ ከውጭ አገር የሚመረቱ ዕቃዎች ውል በመፈጸም ስራ ያልተጀመረ መሆኑ፣ በመሬት ውስጥ የሚቀበሩ ቱቦዎችና መሳሪያዎች የማምረትና የመግዛት አቅርቦት የዘገየ መሆኑ እንዲሁም ለፋብሪካው የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ምርት ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2009 ዓ.ም ሩብ ዓመት ያልተመረተና ልዩነት ያልታየበት መሆኑ፤

154. ምንም እንኳን እነኚህ ጉዳዮች በመጀመሪያው ጥናት ውስጥ መካተት ቢኖርባቸውም ተቋራጩ ተጨማሪ ስራዎችን ማለትም የድንጋይ ከሰልን

በዓመት የማምረት አቅም ከ1.2 ወደ 1.8 ሚሊዮን ቶን ከፍ ለማድረግ፣ በፕሮጀክቱ ሳይት መቀያየር ምክንያት፣ ለፋብሪካው ለመጠጥ፣ ለፕሮሰስ፣ ለመሳሪያዎች ማቀዝቀዣ ለሚያስፈልግ የውሃ ግድብ ስራ፣ ከጅቡቲ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚጓጓዙ የማምረቻ መሳሪያዎች የሚከፈል የትራንስፖርት ወጪ፣ ለሰብስቴሽን ማቋቋሚያ ግንባታ ስራ እና የash and slag handling ስራ አመቺ በሆነ መልኩ ለመገንባት ተጨማሪ ብር 3,415,150,000 የጠየቀ ቢሆንም በፕሮጀክቱ ባለቤት ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ውሳኔ ያልተሰጠው መሆኑ፤

በስኳር ኮርፖሬሽን የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ሥራዎች ውጤታማነትን በተመለከተ

155. በወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ በኮንትራት ውል ሰነድ 1ቢ /Volume- 1B/ እ.ኤ.አ ጥር 21/2008 የጨረታ ሰነድ ስምምነት ሰንጠረዥ ተ.ቁ 9 ላይ ዲዛይንና ዝርዝር የኢንጅነሪንግ ፓኬጅ ተቋራጩ ጨረታውን እንዳሸነፈ ለቀጣሪው ድርጅት ማስረከብ ያለበት መሆኑንና ይህም እንደ ዋና ኢንጅነሪንግ አመልካች ዳታ ሆኖ በኢንፎርሜሽን ሰጪነት ማገናዘቢያ እንደሚያገለግል የተገለፀ ቢሆንም ተቋራጩ በውሉ መሰረት የሚያስፈልጉ የፋብሪካው ንድፎችን /Drawing/ እና ማንዋሎችን ሙሉ ለሙሉ ያላስረከበ መሆኑ ታውቋል፡፡

156. እ.ኤ.አ ጥር 21/2008 በቀጣሪው ድርጅት እና በተቋራጩ በተፈረመው ኮንትራት ውል ስፔሻል ኮንዲሽን /ልዩ ሁኔታ/ በንዑስ ቁጥር ጂ.ሲ.ሲ/ GCC 27.6.1/ ላይ በተመለከተው መሰረት የፋብሪካው የሥራ ዋስትና ፍተሻ /Guarante Test/ ሶስት ጊዜ በሚከናወንበት ወቅት ማንኛውም የፋብሪካው አካል /Equipment/ ውጤታማ ካልሆነ ጥገና ሳያስፈልገው በተቋራጩ ዋስትና አዲስ ተተክቶ የዋስትና ማረጋገጫውም ለአንድ ዓመት እንደሚራዘም የተመለከተ ቢሆንም የወንጂ/ሸዋ አዲሱ የማስፋፊያ ፋብሪካ ሥራውን እንዲጀምር የተደረገው ተቋራጭ የሥራ ብቃት ፍተሻ /Commissioning/ ሳያደርግ መሆኑ ታውቋል፡፡

የልዩ ኦዲት ስራዎች

157. በዕቅድ ከያዝናቸው የኦዲት ሥራዎች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በፍርድ ቤቶች፡ በፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን፣ እንደዚሁም በሌሎች የተለያዩ አካላት ጥያቄ 8 የልዩ ኦዲት ስራዎች ተከናውነው ሪፖርታቸው ለሚመለከታቸው አካላት የተላከ ሲሆን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ

ተወካዮች ም/ቤትና በአዲስ አበባ ከተማ ም/ቤት ጥያቄ የተጀመረው አንድ ሌላ ልዩ ኦዲት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በመ/ቤታችን በተሰጡ የኦዲት ማሻሻያ ሃሣቦች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዱ የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ

158. በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት ኦዲት ተደራጊዎች በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በተላኩ የኦዲት ሪፖርቶች የተገለጹ ግኝቶች ላይ በጊዜ ገደብ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና ለመውሰድ ካልቻሉም ምክንያቱን በመግለፅ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማሳወቅ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡

159. በዚሁ መሠረት የ2008 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ወቅት በ2007 ኦዲት ላይ በተደረገው የክትትል ኦዲት 55 መ/ቤቶች እና 19 ቅ/ጽ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

160. በሌላ በኩል ከ2002 እስከ 2006 በተደረጉ ኦዲቶች ከደንብና መመሪያ ወጭ ክፍያዎች ያላግባብ በመፈጸማቸው ገንዘቡ ለመንግሥት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ ከተባለው ብር 331,090,460.02 ውስጥ ተመላሽ የተደረገው ብር 17,078,726.13 ወይም 5.16% ብቻ መሆኑን መ/ቤቶቹ በውስጥ ኦዲተሮቻቸው አረጋግጠው ከላኩልን መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ጊዜ የተለያዩ እቃ አቅራቢዎችና ተቋራጮች በገቡት ውል መሠረት ባለመፈጸማቸው እንዲሰበሰብ ከተባለው ብር 325,064,647.71 ውስጥ የተሰበሰበው ብር 394,228.36 ወይም 0.12% መሆኑ ታውቋል፡፡ በአጠቃላይ ያላግባብ ክፍያ በመፈጸሙ እንዲመለስና ከቅጣት እንዲሰበሰብ ከተባለው ብር 656,155,107.73 ውስጥ የተመለሰውና የተሰበሰበው ብር 17,472,954.49 ወይም 2.66% ብቻ ነው፡፡ ይህ መ/ቤቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት ተገቢና በቂ እርምጃ እየወሰዱ አለመሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በመሆኑም የተከበረው ምክር ቤትና መንግሥት ህግና ሥርዓት እንዲከበር ያላግባብ የተከፈለው የመንግስት ገንዘብ እንዲመለስ ተገቢውን እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

161. በአጠቃላይ ሲታይ በኦዲት ግኝቶች ላይ እርምጃ የመውሰድና የማስተካከል ዝንባሌ በተወሰነ ደረጃ በተወሰኑ መ/ቤቶች መሻሻል የሚያሳይ ቢሆንም ገና ወደሚጠበቀው ደረጃ ሊቀርብ አልቻለም፡፡ ይህን ሁኔታ ለመለወጥ መ/ቤታችን ከሚያደርገው ጥረት ጎን ለጎን የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጠንካራና ተከታታይ

ይፋዊ መድረክ በማዘጋጀት ኦዲት ተደራጊዎችን ስለወሰዱት እርምጃ መጠየቁና ሌሎችም የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ አባላት የሚከታተሏቸው መ/ቤቶች በኦዲት ግኝት ላይ የወሰዱትን እርምጃ በጥብቅ እየተከታተሉ በመሆኑ ኦዲት ተደራጊዎች እርምጃ እንዲወስዱ ጫና እየፈጠረ ይገኛል፡፡ እንደዚሁም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ከዚህ አንፃር እያደረገ ያለው ክትትልም የራሱን ተፅዕኖ በማሳደር ላይ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ይህ ሁሉ ጫና ወደሚታይ ተጨባጭ እርምጃ ባለመሸገሩ አንዳንዶቹ ከምንም እየቆጠሩት አይደለም፡፡

162. በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 አንቀፅ 25 ንዑስ አንቀፅ 1 (መ) መሠረት ያለበቂ ምክንያት በፌዴራል ዋና ኦዲተሩ በቀረቡ የኦዲት ሪፖርቶች በተሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶችና ሃሣቦች ላይ በወቅቱ እርምጃ ያልወሰደ፤ ወይም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት መፈጸም ሲኖርበት ለመፈጸም ፈቃደኛ ሆኖ ያልተገኘ በህግ እንደሚቀጣ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም ኦዲት ተደራጊዎች በዚህ መልኩ ከሚደርስ ተጠያቂነትና ቅጣት ለመዳን አሁንም በአስቸኳይ ተገቢውን እርምጃ ሊወስዱና የተዘረጋውን አሠራርና ሥርዓት አክብረው ሊሠሩ ይገባል፡፡

የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ

163. በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የለውጥ ሥራውን በሚገባ ለመተግባር በመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ ሲሠሩ የነበሩት የካስኬድንግ፣ ውጤት ተኮር ሥርዓትን መሠረት ያደረጉ የስትራቴጂክ ዕቅድና የአመታዊ ዕቅድ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቅቀው ጉድለቶች ቢኖሩትም በድጋፍ ዘርፉ የሥራ ክፍሎች የውጤት ተኮር ሥርዓቱ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ በኦዲት ዘርፉ ግን ተገቢ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች ባለመጠናቀቃቸው ዘግይቶ በዚህ ዓመት በመጋቢት ወር ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ ይሁንና በሁለቱም ዘርፎች የምዘና ሥርዓቱን በቴክኖሎጂ የማስደገፍና የምዘና ሂደቱን የማቅለልና የማቀላጠፍ ሥራዎች ግን ገና በጅምር ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡

164. የመልካም አስተዳደር ጉዳዮችን በተመለከተ በመ/ቤታችን ተለይተው የነበሩት ከአሠራር ጋር የተያየዙ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በአብዛኛው የተፈቱና መሻሻል የታየባቸው ቢሆንም ከብቃትና ክህሎት እንደዚሁም ከአመለካከት ጋር የተያያዙት ችግሮች ግን አሁንም በቀጣይነት እየተሠራባቸው ይገኛሉ፡፡

ሴክተር ዘለል ሥራዎችን በተመለከተ

165. በዚህ ረገድ የሥርዓተ ፆታ ሥራዎችን በተመለከተ በሁሉም ሥራዎቻችን አካተን ለመፈጸም ሁሉም የሥራ ክፍሎች የሥራ ዕቅዳቸው አካል እንዲያደርጉ ተደርጓል፡፡ በተለይ የኦዲት ዕቅዳችንም አንዱ አካል በማድረግ በ2008 ኦዲት ወቅት የአፈርማቲቭ አክሽን በሁሉም መ/ቤት በተገቢው የተተገበረ መሆኑን በኦዲታችን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

166. በሌላ በኩል እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ዓለም አቀፍ የሴቶችና የፀረ-ጾታ ጥቃት ቀናትን የተለያዩ ትምህርታዊና የግንዛቤ ማዳበሪያ ዝግጅቶችን በማድረግ በቅንጅት ተከብሯል፡፡ በሌላም በኩል በየሁለት ወሩ የሚካሄደው የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኖች የሚገናኙበትና ልምድ የሚለዋወጡበት መድረክ ቋሚ መተዳደሪያ ደንብ እንዲኖረው ተደርጓል፡፡

167. በተጨማሪም አነስተኛ የገቢ ምንጭና ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ላላቸዉ የመ/ቤቱ 30 ሴት ሰራተኞች መሰረታዊ የንግድ ክህሎት ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በግማሽ ክፍያና ነጻ የርቀት ትምህርት ዕድል በማፈላለግ 10 ሴት ሠራተኞች በዲፕሎማ፣ 11 ሴት ሠራተኞች በዲግሪ እንዲሁም 5 ሴት ሠራተኞች ከ5ኛ-7ኛ ክፍል በገንዘብ ሲተመን ብር 105,150.00 ለሠራተኞች ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

168. HIV/AIDSን በተመለከተ የተለያዩ የሠራተኛ መድረኮችንና ጽሁፎችን በማዘጋጀትና በፊት ለፊት መድረኮችና በመ/ቤታችን በተዘረጋው የመረጃ ቴክኖሎጂ አማካይነት ሁሉንም ሠራተኛ ባዳረሰ መንገድ ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ፡፡

የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በተመለከተ

169. የመ/ቤቱንና የሠራተኛውን አቅም ከመገንባት አንፃር ሦስት ጉዳዮችን ማዕከል በማድረግ የአቅም ግንባታ ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው፡፡

170. የመጀመሪያው የሠራተኛውን ብቃትና ክህሎት የማሳደግ ጉዳይ ሲሆን ከዚህ አንፃር በመ/ቤታችን አዲሱ ህንፃ ውስጥ አንድ ወለል ለማሠልጠኛ ማዕከልነት በመለየት ክፍሎቹን በተገቢው መሣሪያ የማደራጀትና በአማካሪዎች አማካይነት ሥልጠና የሚሰጥባቸውን ማቴሪያሎች የማዘጋጀት ሥራ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡ ማዕከሉ የክልል ዋና ኦዲተሮችንም ጭምር አቅም ለመገንባት የሚያገለግል ይሆናል፡፡

171. ሁለተኛው የመ/ቤቱ የዳታ ማዕከል የመገንባትና ሁሉንም ሥራዎቻችንን በቴክኖሎጂ በማስደገፍ የሥራና አሠራር ቅልጥፍናን የማሳደግ፤ የአሠራር ወጥነት ለማስፈንና የወረቀት፤ የቀለምና ተያያዥ የጥገና የግንኙነት ወጪዎችን ጭምር የመቀነስ ሲሆን ለዚህ ማስተር ፕላን ተዘጋጅቶ የዳታ ማዕከሉ መሣሪያዎች ግዢና ሌሎች አስፈላጊ ተግባራት እየተፈጸሙ ይገኛል፡፡ ይህ በቅርቡ እንደሚጠናቀቅና ሙሉ በሙሉ እንደሚተገበር የሚጠበቅ ሲሆን በአሁኑም ሰዓት ቢሆን Corporate e-mail system እና Outlook የሚባለውን ሥርዓት በመጠቀም በመ/ቤቱ ውስጥ የሚደረጉ ግንኙነቶችን ወደ ቴክኖሎጂ በመለወጥ የወረቀትና የቀለም ወጪን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ ተችሏል፡፡

172. ሦስተኛው የአቅም ግንባታ ማዕከል የኦዲት ጥራትን የማጎልበት ሥራ ሲሆን ከዚህ አንጻር የመ/ቤታችን የኦዲት ጥራት አሁን የሚገኝበት ደረጃ (Baseline) በእንግሊዝኛ ተናጋሪ የአፍሪካ ሀገሮች ዋና ኦዲተሮች ማህበር አማካይነት ከተለያዩ አባል ሀገራት ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች በተውጣጡ ከፍተኛ የኦዲት ባለሙያዎች አሁን የምንገኝበት ደረጃ ተለይቷል፡፡ ይህንን መሠረት በማድረግ በሚቀጥሉት አራት ዓመታት በመስክ ጭምር ከኦዲተሮቻችን ጋር እየሠራ የኦዲተሩን ብቃትና ክህሎት በማሳደግ ኦዲቶቻችን በእርግጥም ዓለም አቀፍ ስታንዳርድን መሠረት አድርገው በሚፈለገው ጥልቀት በመፈጸም ከአሁን በተሻለ ሁኔታ በየመ/ቤቶቹ የሚታዩትን የአሠራር ግድፈቶችንና ክፍተቶችን የመለየት አቅም የሚፈጥር ልምድ ያለው የኦዲት አማካሪ ድርጅት የሚቀጠር ይሆናል፡፡ የዚህም አማካሪ ድርጅት የመቅጠር ሂደት ጨረታ ወጥቶ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሁኔታ

173. ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል ለኦዲት ባለሙያ 645 እና ለድጋፍ ሰጪ 314 በድምሩ 959 ሲሆን በየካቲት ወር 2008 የኦዲት ሥራው ሲጀመር የነበረው የሰው ሀይል 265 ኦዲተሮችና 145 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ 413 ነበር፡፡ በኦዲት ዓመቱ 156 ኦዲተሮችና 89 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በድምሩ 245 ሠራተኞች የተቀጠሩ ሲሆን፣ ከድጋፍ 7 እና ከኦዲት 4 ሠራተኞች በጡረታ የተገለሉ፣ 1 በሞት የተለዩ፣ 21 ኦዲተሮችና 21 ድጋፍ ሰጪ በድምሩ 42 ሠራተኞች በራሣቸው ፈቃድ መ/ቤቱን የለቀቁ ሲሆን በአጠቃላይ በኦዲት ዓመቱ 54 የሰው ኃይል ከመ/ቤቱ ለቀዋል፡፡

174. በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ የኦዲት ባለሙያዎች 265 ወንዶችና 135 ሴቶች በድምሩ 400፣ የድጋፍ ሰጪ 89 ወንዶችና 115 ሴቶች በድምሩ 204 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በአጠቃላይ 604 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ የነበሩ ሲሆን 355 የሥራ መደቦች በክፍትነት ተመዝግበው ይገኛሉ፡፡ እነኚህ ክፍት የሥራ መደቦችን ለመሙላት በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

የ2008 በጀት ዓመትና 2009 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር የበጀት አጠቃቀም

175. በ2008 በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱ ሥራዎች ማከናወኛ ብር 44,149,612.69 በጀት ተፈቅዶ ብር 42,142,107.21 ወይም 95.4% ሥራ ላይ የዋለና ያልተሰራበት ብር 2,007,505.48 (4.6%) የነበረ ሲሆን፣ ለ2009 በጀት ዓመት ዕቅድ ማስፈጸሚያ ለመ/ቤታችን ከተፈቀደው ብር 79,290,102.00 ውስጥ እስከ መጋቢት 30/2009 የነበረው የዘጠኝ ወር በጀት ብር 59,295,076.50 ሲሆን በዘጠኝ ወር ውስጥ ስራ ላይ የዋለው ደግም ብር 50,407,678.96 ወይም 85.00% ሆኗል፡፡

መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች

176. መ/ቤታችን በሕገ-መንግሥቱና የማቋቋሚያ አዋጁ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ቢሆንም፤ በሥራ ሂደት እየተፈታተኑን ከሚገኙ ተግዳሮቶች መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

177. በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ መሠረት ሁሉም መ/ቤቶች ሂሳባቸውን የበጀት ዓመቱ እንዳለቀ እስከ መስከረም 30 ዘግተው ሂሳቡን ለኦዲት ማቅረብ ቢኖርባቸውም 72 መ/ቤቶች ወይም 46.83% የሚሆኑት ሂሳባችውን ከመስከረም 30/2007 ዓ.ም በኋላ ከጥቅምት1/2009 እስከ ጥር 24/2009 ዓ.ም ድረስ አዘግይተው ለኦዲት ያቀረቡ በመሆኑ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በታሰበው ጊዜ ማጠናቀቅ አላስቻለንም፡፡ በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ሂሳቡን ዘግተናል ብለው ከሰጡን መ/ቤቶችም ውስጥ የማይናቅ ቁጥር ያላቸው አልዘጉም ተብሎ ስማቸው እንዳይነሣ እንጂ መረጃዎችን በሚገባ አሟልተው የሰጡን ባለመሆኑ ሥራችንን በወቅቱ በዕቅዳችን መሠረት እንዳናጠናቅቅ ከፍተኛ ተጽዕኖ አድርጎብናል፡፡

178. በአጠቃላይ ሲታይ ለኦዲቱ ሥራ የሚደረገው ትብብር መሻሻል ያሳየ ቢሆንም አሁንም አልፎ አልፎ የሥራ ቦታ ያለማመቻቸትና ማስረጃ ያለመስጠት፣ ለኦዲት ማስታወሻዎች በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠት፣ ኦዲተሮች ሥራቸውን አጠናቀው የመውጫ ስብሰባ አድርገው ከወጡና ወደ ሌላ ሥራ ከተሰማሩ በኂላ በኦዲት ወቅት ያላቀረቧቸውን ማስረጃዎች አሉን በማለት መ/ቤታችን ድረስ ይዘው የማምጣት፣ በመጀመሪያው የመውጫ ስብሰባ ላይ ባለመገኘት ድጋሚ እንዲደረግ የመጠየቅ፣ ለረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት በወቅቱ ምላሽ ያለመስጠትና የመውጫ ስብሰባ ከተደረገ በኂላ በርካታ በኦዲቱ ወቅት ሊቀርቡ ይችሉ የነበሩ ማስረጃዎችን የማቅረብ ሁኔታዎች የሚታዩ በመሆኑ መ/ቤቶቹ በፍጥነት እነኚህን ችግሮች በማስወገድ ሕጋዊ ኃላፊነታቸውን በተገቢው ጊዜ ሊወጡ ይገባል።

የ2009/2010 ኦዲት ዓመት ዕቅድ

179. ለሰው ሀይል ፍልሰቱ ምክንያት መንስዔ የሆነው ችግር በመቀረፉ ያሉት ክፍት የስራ መደቦች እንደሚሟሉ ታሳቢ በማድረግ በ2009 በጀት ዓመት ሂሳብም የኦዲቱ ሽፋን 100% ሆኖ እንዲቀጥል የ174 መስሪያ ቤቶች ሂሳብ ላይ የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ለማድረግ ታቅዷል። ካለፉት ዓመታት በተለየ ሁኔታ የኦዲት ጥራት የሁሉም ኦዲት ፈፃሚ ልዩ ትኩረት እንዲያገኝ ተደርጎ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ዕቅድ ተነድፏል። በሌላም በኩል ከመጋቢት 2009 እስከ ጥር 2010 ዓ.ም ድረስ 20 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶችንና 8 የክትትል ኦዲቶችን በማከናወን 28 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችን ለማውጣት ታቅዷል። በተጨማሪም በ250 የመሠረታዊ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆኑ ወረዳዎችና የሴክተር ቢሮዎች የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ ለማከናወን እንደዚሁም አንድ ፕሮግራም አቀፍ ኦዲት በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ደረጃ ለማካሄድ በእቅድ ተይዟል።

በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወነ ኦዲት

180. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ኃላፊነት ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የዕርዳታ ሂሳቦችን በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በማስደረግ ላይ ይገኛል። በዚሁ መሠረት በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት አስደርጎ በሚቀርቡ ሪፖርቶች መነሻነት አስፈላጊ የማሻሻያ እርምጃዎችን እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊ ድርጅቶች፣ ለሥራ አመራር ቦርድና ለተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ማሳሰቢያ ተሰጥቷል።

181. በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በ2008 እና ሪፖርቱን ወቅታዊ ለማድረግ እስከ ታህሳስ 30/2009 ዓ.ም በተከናወኑና ለመ/ቤታችን በደረሱን ኦዲቶች የታዩ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች በዋና ኦዲተር መ/ቤት ዘገባ ጥራዝ 2 ክፍል 3 በዝርዝር የቀረቡ ስለሆነ ዝርዝሩን ከዚያው መመልከት ይቻላል።

ኦዲት የተደረጉ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች የሂሣብ መግለጫዎች ላይ የተሰጠ የኦዲት አስተያየት

182. በ2008 በጀት ዓመት እና ሪፖርቱን ወቅታዊ ለማድረግ እስከ ታህሳስ 30/2009 ዓ.ም ኦዲት ተደርገው የተከናወኑና ከሐምሌ 2007 እስከ ጥር 2009 ዓ.ም አንድ ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ (ቀደም ሲል እስከ ሰኔ 30 የደረሱንን ብቻ ነበር ስናቀርብ የነበረው) ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን የቀረቡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 113 ሲሆኑ በኢትዮጵያ መንግሥትና በአጋር ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት 192 በድምሩ 305 (ይህ ቁጥር በጊዜው የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገ ድርጅት ወይም ፕሮጀክት ውስጥ የቅርብ ዓመቱን እንደ አንድ ብቻ በመቁጠር የተወሰደ ነው) ናቸው።

183. በእነዚህ ሪፖርቶች ላይ የተሰጠው የኦዲት አስተያየት ዓይነት ሲተነተን አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified Opinion) 203፣ ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት (Qualified Opinion) 69፣ አቋም ለመውሰድ እንደማይቻል በመግለፅ አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer Opinion) 29፣ አጥጋቢ ሆነው ባለመገኘታቸው የተቃውሞ አስተያየት የቀረበባቸው (Adverse) 1፤ የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠበት ኢንቲሪም ኦዲት 2 እና ሌሎች 1 በድምሩ 305 ናቸው።

184. በሌላም በኩል መ/ቤታችን ባለው መረጃ መሠረት ሂሣባቸውን ዘግተው ኦዲት ያላስደረጉ 50 የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ይገኛሉ።

የኮርፖሬሽኑ የዕቅድ ክንውን

185. በ2008 በጀት ዓመት መጀመሪያ በነበረው 143 (99 ኦዲተሮችና 44 ድጋፍ ሰጪ) የሰው ኃይል 260 ኦዲቶችን ለማከናወን አቅዶ 238 ኦዲቶችን ወይም ከዕቅዱ በታች 22 (8%) የፈጸመ ሲሆን ለዚህም ዋና ምክንያቱ በቁጥር 49 ረቂቅ ኦዲት ሪፖርቶች ለደንበኞች ተልከው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ምላሽ ያልተሰጠባቸው በመሆኑ ነው፡፡

የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ

186. ኮርፖሬሽኑ በ2008 በጀት ዓመት ከኦዲት ሥራ አገልግሎት ብር 28,994,382.00 ገቢ ለማግኘት አቅዶ ብር 33,920,965.00 ገቢ አግኝቷል፡፡ በሌላም በኩል ብር 24,650,964.00 ወጪ ለማድረግ አቅዶ ብር 22,299,745.00 ወጪ ያደረገ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ብር 5,078,494.00 የተጣራ ትርፍ ሊያገኝ ችሏል፡፡

ማጠቃለያ

187. በሪፖርቱ እንደተመለከተው በ2008 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የተካሄደው ኦዲት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የተያዙትን ጨምሮ የሁሉም የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ኦዲት የተደረጉ በመሆኑ የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ዕቅዱን መቶ በመቶ መፈጸም የተቻለ ከመሆኑም በላይ ባለፉት ዓመታት የተረጋገጠውን የ100% የኦዲት ሽፋን አፈጻጸም ለማስቀጠል ተችሏል፡፡

188. የክዋኔ ኦዲት ዕቅድ አፈጻጸምም ቢሆን 18 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲትና 8 የክትትል ኦዲት በማከናወን 26 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ለማውጣት ታቅዶ 18 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲትና የ7 ክትትል ኦዲት ሪፖርቶችን ጨምሮ 25 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ወጪ ተደርገዋል፡፡ በቀሪው 1 የክትትል ኦዲት ምትክ ሌላ አዲስ የክዋኔ ኦዲት ተጀምሮ የተጠናቀቀ ሲሆን የመውጫ ስብሰባ ብቻ ባለመደረጉ ሪፖርቱ ወጪ አልሆነም፡፡ ይህን ሣይጨምር የዕቅድ ክንውኑ 96.15% ነው፡፡

189. የመሠረታዊ አገልግሎት ከለላ ኦዲትን በተመለከተ በ305 ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በክልልና ዞን ደረጃ በሚገኙ ፈጻሚ ሴክተር ቢሮዎች ኦዲቱን ለማከናወን ታቅዶ በ238 (78%) ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በክልልና ዞን ደረጃ በሚገኙ ፈጻሚ ሴክተር ቢሮዎች ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡ በሌላ በኩል በዕቅድ ወቅት ያልታወቀና በዕቅድ ያልተያዘ ነገር ግን ለመንግሥት ለሚደረገው የገንዘብ ፍሰት የኦዲት ሪፖርታችንን መሠረት የሚያደርገው በፍትሃዊ መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ አቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Services-ESPES, Program for Result) የገንዘብ ፍሰት አመልካቾችን የማረጋገጥ ሥራ (Verfication) በ64 ወረዳዎች በመከናወኑ አጠቃላይ ክንውኑን 302 ወረዳዎች ወይም የዕቅዱ 99.02% መፈጸም ተችሏል፡፡

190. በአሁኑ ወቅት ሁሉም የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች በየዓመቱ ኦዲት እየተደረጉ በየተቋማቱ የሚታዩ የፋይናንስ አስተዳደርና የንብረት አጠቃቀም ክፍተቶች እየተለዩ ቢሆንም በሚመለከታቸው መ/ቤቶች ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ በበቂ ደረጃ እርምጃ ባለመወሰዱ ከሞላ ጎደል በየዓመቱ ተመሳሳይ ጉዳዮች ግኝት ሆነው በመታየት ላይ ናቸው፡፡ በቂ ትኩረት ቢሰጣቸው ኖሮ እነዚህ ጉድለትና ክፍተቶች ሊታረሙ የሚችሉ ናቸው፡፡

191. ስለሆነም የሚመለከታቸው ሁሉ የተጠናከረ ክትትል ሊያደርጉና ተገቢውን እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡ ዝርዝር የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቱና ዘገባ በሁለት ጥራዝ እንደዚሁም የእያንዳንዱ ክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ሪፖርት ደግሞ በ24 ጥራዝ ተዘጋጅቶ ለተከበሩ አፈ-ጉባዔ የተላከ በመሆኑ ሪፖርቶቹን በምክር ቤቱ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም ቋሚ ኮሚቴዎች ጭምር በጥልቀት በመመርመር እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

192. በዚህም ምክንያት እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ በ2008 በጀት አመት ሂሳብ ኦዲትም ወቅት የውዝፍ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣቦች፣ ደንብና መመሪያን ሳይጠብቁ የሚፈጸሙ ግዥዎች፣ ከመንግሥት የግንባታ ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ በወቅቱና በተያዘላቸው በጀት ያለመጠናቀቅ፤ ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ በየዓመቱ የሚታዩ ተደጋጋሚ ችግሮችና ከውስጥ ገቢ አሰባሰብ፣ አጠቃቀምና ሪፖርት አደራረግ አንፃር የሚታዩ ችግሮች እንደዚሁም በመንግሥት ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮች አሁንም ዋነኛ ግኝቶች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በመሆኑም እነኚህን ችግሮች በመጠኑም ቢሆን ሊያቃልሉ እንደሚችሉ የታመነባቸው የሚከተሉት የመፍትሄ ሃሳቦች ተጠቁመዋል፡፡

193. ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ የመጀመሪያው እርምጃ አዳዲስ ውዝፎች እንዳይፈጠሩ ጥብቅ የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶና መ/ቤቶች ኃላፊነት ወስደው እንዲፈጽሙ ማድረግና ሥርዓቱንም ለበጀት ጥያቄ እንደቅድመ ሁኔታ መጠቀም፡፡

194. የቆዩ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ ጊዜ ገደብ ተቀምጦ በተቀመጠው አሠራር መሠረት እንዲሰበሰብ ወይም እንዲከፈል ወይም እንዲወራረድ ወይም ከመዝገብ እንዲሠረዝ እንዲደረግ ነገር ግን በዚህ መሠረት መፍትሄ ማምጣት ካልተቻለ ለምን በተቀመጠው አሠራር ሂሳቦቹን መሰብሰብ ወይም መክፈል ወይም ማወራረድ ወይም ከመዝገብ መሠረዝ እንዳልተቻለ ዝርዝር መረጃ ተሰብስቦና ተጣርቶ ሌሎች አማራጭ እርምጃዎችን መውሰድ፤

195. ከመንግሥት ገቢ አተማመንና አሰባሰብ ጋር ተያይዞ የሚታዩ ችግሮችን በተመለከተ በጅምር ላይ ያሉ የቴክኖሎጂ አማራጮችን በማስፋት የታክስ መረጃ አያያዝና አስተዳደር ሥርዓትን ማዘመን፤ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀምን ማሳደግ፤ ያለደረሰኝ የሚደረጉ ግብይቶች በደረሰኝ ብቻ የሚሆኑበትን ሥርዓት አስገዳጅ ማድረግና መተግበር፤ ወደ ግብር መረብ ያልገቡትን ማስገባት፤ ህጋዊ ያልሆኑ ንግዶችን ኮንትሮባንድን

ጨምሮ ዘላቂ በሆነ ሥርዓት መቆጣጠር፤ በቀጣይነት የህብረተሰቡ ግንዛቤ ላይ መሥራት እና የገቢ ሰብሳቢ ተቋማትን አቅም መገንባት፤

196. ከግንባታ ጋር ተያይዞ የሚከተሉት እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡፡ በመጀመሪያው ደረጃ ለፕሮጀክቶች በጀት ከመፈቀዱ በፊት በበቂ ጥናት ላይ የተመሠረቱ የተሟላና የተረጋገጠ ዲዛይን ያላቸው እንዲሁም ግልፅና ተጨባጭ የትግበራ መርሀ ግብር የተዘጋጀላቸው መሆኑን በማረጋገጥ ብቻ በጀት ሊፈቀድ ይገባል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ ጥብቅ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ኖሯቸው ሊመሩ ይገባል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ በማንኛውም የመንግሥት ግንባታ (በፌዴራልም ይሁን በክልል) ላይ የሚሳተፉ ተቋራጮችና አማካሪዎች አፈፃፀም (ከጥራትና ከጊዜ ጭምር) በማዕከላዊ የዳታ ቋት ተቀምጦ አዳዲስ የግንባታ ኮንትራት ለመስጠት እንደ አንድ መሠረታዊ መስፈርት ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር አሁን በግንባታ ፕሮጀክቶች አካባቢ የሚታዩትን ችግሮች በማቃለል ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡

197. በተመሳሳይ ሁኔታ ዕቃና አገልግሎት ለማቅረብ ውል ገብተው በተባለው ጥራትና ጊዜ የማያቀርቡትን አቅራቢዎችን ለመቅጣት የተዘረጋ የአሠራር ሥርዓት ቢኖርም በብዙዎቹ የመንግሥት መ/ቤቶች ባለመተግበሩና አደገኛም በመሆኑ ይህን በማይተገብሩ መ/ቤቶችና ኃላፊዎች ላይ ተገቢው አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ አሁን የሚታየውን ችግር ከመፍታት አንፃር ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

198. ከመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ጋር ተያይዞ ስታንዳርድ ያልወጣለት በመሆኑ መንግሥትን ከፍተኛ ወጭ እያስወጣ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ምን ዓይነትና ደረጃ ያላቸው የመስተንግዶ አገልግሎቶች በየትኛው ደረጃ ይስተናገዱ የሚለውን በተመለከተ ደረጃ ቢወጣላቸውና የግዥ ዘዴውም ጭምር በተለየ ሁኔታ ቢዘረጋ በየዓመቱ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሱትን ክፍተቶች ለማረም የሚያስችል ይሆናል፡፡

199. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን በተመለከተ ለበርካታ ኦዲት ግኝት እምብርት የሆኑትን በተቋማቱ ከሚከናወኑት ግንባታዎች እንዲሁም የዕቃና የአገልግሎት ግዢዎችን በተመለከተ ሌሎች አማራጮች ቢፈተሹና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ በመማር መስተማርና በምርምር ሥራ ላይ ብቻ አተኩረው እንዲሠሩ ቢደረግ፤ በሌላ በኩል ግልፅ ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ወይንም በሚመለከታቸው አካላት የጋራ ስምምነት ባለመደረሱ በየዓመቱ የሚታዩ የኦዲት ግኝቶችን በተመለከተ ከፍተኛ

ትምህርት ተቋማት፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጋር ሆነው በአስቸኳይ መፍትሄ እንዲበጅለት ቢደረግ፡፡

200. የመንግሥት ንብረት አያያዝን በተመለከተ መጠነኛ መሻሻል የሚታይ ቢሆንም የንብረት አወጋገድ ግን አሁንም ልዩ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡ በተለይ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች አወጋገድ በቂ ትኩረት ተሰጥቶት ባለቤትም ኖሮት እየተሠራ አይደለም፡፡ የተለያዩ ኬሚካሎችም አወጋገድ ጉዳይ ከኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ሌሎችም ዕቃዎች ቢሆኑ በመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎትና በተቋማቱ መካካል አንዱ በአንዱ ላይ በማሳበብ ንብረቶቹ ሳይወገዱ ከፍተኛ ክምችት በተለይ ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ መ/ቤቶች ይታያል፡፡ ስለሆነም የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎትን አቅም ማሳደግ ወይም ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ሌሎች አማራጮችን ጭምር ማየቱ ጠቃሚ መሆኑ ይታመናል፡፡

201. በየአመቱ ባደረግናቸው ኦዲቶች ያላግባብ የፈጸሙትን ክፍያ እንዲያስመልሱና ከተዘረጋው የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ውጭ እየተፈጸሙ ያሉ ተግባራት እንዲያቋርጡ በተደጋጋሚ አሳስበን ያልፈጸሙ ተቋማትና በየደረጀው ያሉ ኃላፊዎቻቸው ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ በፍጥነት ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር አሁን የጀመረውን በጎ ጅምርና ጥረት ሊያጠናክር ይገባል፡፡ በሌሎች አካላትም ተጨባጭ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡፡

202. መሻሻል ሲገባው አሁንም ያልተሻሻለው የባለበጀት መ/ቤቶች ሂሳብን በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ ዘግቶ ለኦዲት ያለማቅረብ ጉዳይ በአንክሮ ሊታይ የሚገባውና ተገቢ እርምጃ የሚያሻው ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህ ጉዳይ የፋይናንስ፣ ግዢና ንብረት ተግባራትን ከሚያከናውኑ ሠራተኞችና ኃላፊዎች አቅምና አቅርቦትም ጋር የሚያያዝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ይህ ሁኔታ በዚህ መልክ ሊቀጥል ስለማይገባ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ አቅም የመገንባትና አቅርቦቱን የማሻሻል ጉዳይ ትኩረት ተሰጥቶት የሚመለከታቸው አካላት ሊሠሩበት ይገባል፡፡ በአጭሩ ጊዜ ግን ይህ ጉዳይ የኦዲት ጥራትና ጥልቀቱም ላይ ተፅዕኖ እያመጣ በመሆኑ በምክር ቤቱም ሆነ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተገቢው አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

203. በመጨረሻም የሚደረገው ኦዲት የአሠራር ክፍተቶችን በማረም

ተጠያቂነትንና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ረገድ የበለጠ አስተዋፅኦ እንዲያደርግና እሴት እንዲጨምር በኦዲት ማሻሻያ አስተያየቶች መሠረት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ፤ ያላግባብ የተከፈለው የመንግሥት ገንዘብ እንዲመለስ፤ ከተዘረጋው አሠራርና ሥርዓት ውጭ በመሆናቸው እንዲቋረጡ የተባሉት ተግባራት በፍጥነት እንዲቆሙ እና አሠራርና ሥርዓት እንዲዘረጋላቸው የተባሉት እንዲፈጸሙ ሁሉም የሚመለከተው አካል ተገቢውን ግፊትና ክትትል እንዲያደርግ በድጋሚ እየጠየቅሁ በጥሞና ስላዳመጣችሁኝ ከልብ አመሠግናለሁ፡፡

አባሪ-1

ሀ/ ሂሳባቸውን በወቅቱ ያልዘጉና ዘግይተው ለኦዲት ያቀረቡ መ/ቤቶች

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን
		የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	
1	1	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት	15/05/2009
		የፋይናንስና ኮሙዩኒኬሽን መ/ቤቶች	
2	1	ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ	12/3/2009
3	2	የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን	8/2/2009
4	3	የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን	15/03/09
5	4	የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት	7/3/2009
6	5	ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት ኤጀንሲ	13/03/09
7	6	ብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን	19/03/09
8	7	የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት	3/4/2009
9	8	ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር	23/03/09
10	9	የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን	30/2/09
11	10	ብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን	29/02/09
12	11	የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ ገቢና ወጪ ሂሳብ	
		የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	
13	1	ትምህርት ሚኒስቴር	3/5/2009
14	2	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	8/3/2009
15	3	ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ	17/02/09
16	4	ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ	19/03/09
17	5	ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ	15/04/09

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን
18	6	አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	5/2/2009
19	7	አምቦ ዩኒቨርሲቲ	1/2/2009
20	8	ዲላ ዩኒቨርሲቲ	20/03/09
21	9	ወለጋ ዩኒቨርሲቲ	13/03/09
22	10	አክሱም ዩኒቨርሲቲ	2/2/2009
23	11	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	15/02/09
24	12	ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ	15/02/09
25	13	ሠመራ ዩኒቨርሲቲ	15/02/09
26	14	የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል	20/02/09
27	15	አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ	3/4/2009
		የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	
28	1	የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር	23/5/2009
29	2	የማዕድን፣ ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር	7/2/2009
30	3	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	10/2/2009
31	4	የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር	19/3/2009
32	5	የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር	3/2/2009
33	6	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	14/2/ 2009
34	7	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን	10/2/2009
35	8	የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን	10/2/2009
36	9	የኢትዮጵያ ጤና መድኅን ኤጀንሲ	14/3 2009
37	10	የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን	10/2/2009
38	11	የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር	17/5/2009
39	12	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት	12/4/2009

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን
		የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	
40	1	አሶሳ ዩኒቨርሲቲ	10/4/2009
41	2	ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ	15/02/09
42	3	ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ	19/03/09
43	4	ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር	26/03/09
44	5	ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ	19/05/09
45	6	የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር	15/05/09
46	7	የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ. ዩኒቨርሲቲ	18/04/09
47	8	የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ	15/03/09
48	9	የኢትዮጵያ የብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት	7/4/2009
49	10	የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት	2/2/2009
50	11	የብሔራዊ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት	12/3/2009
51	12	ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ	25/02/09
52	13	የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት	10/4/2009
53	14	የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ	19/3/09
54	15	የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር	17/04/09
55	16	የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር	9/5/2009
		የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	
56	1	የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር	24/4/09
57	2	ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት	3/5/2009
58	3	ንግድ ሚኒስቴር	2/3/2009
59	4	የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን	2/2/2009
60	5	የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት	26/3/09
61	6	የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	24/2/2009

ተ.ቁ		የመ/ቤቱ ስም	የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን
62	7	የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም	21/2/2009
63	8	የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት	14/2/2009
64	9	የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	8/3/2009
65	10	የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ልማት ኢንስቲትዩት	9/2/2009
66	11	የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	13/03/2009
67	12	የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	24/05/2009
68	13	የፌዴራል የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን	23/02/2009
69	14	የፌዴራል በጎ አደራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ	2/3/2009
70	15	የኢትየጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን	13/4 /2009
71	16	ጠቅላይ ፍ/ቤት	21/4/2009
72	17	የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት	23/02/2009

አባሪ-2

በ2008ና ባለፉት ሶስት ኦዲቶች ሂሣባቸው የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸው/X/ ወይም አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች/XX/

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	2008	2007	2006	2005
	የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች				
1	የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት	XX			
	የፋይናንስና ኮሙዩኒኬሽን መ/ቤቶች				
2	የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን	XX			
	የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች				
3	የሀገር መከለከያ ሚኒስቴር	XX	XX	XX	XX
4	የብሔራዊ መረጃ ደህንነት አገልግሎት	XX	XX	X	X
	የፋይናንስና ኮሙዩኒኬሽን መ/ቤቶች				
5	የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን	X			
6	የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር	X			
7	የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት	X			
8	**የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች**				
9	የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	X	X	X	X
10	**የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች**				
11	የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር	X	X	X	X
12	የኢትዮጵያ መድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን	X	X	X	
13	የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ	X			
14	የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር	X			
15	የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	X			
16	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	X			
17	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	X			
18	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	X	X	X	
	የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት				
19	ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X	
20	ሠመራ ዩኒቨርሲቲ	X			
21	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X	X
22	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X	XX
23	ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ	X			
24	አክሱም ዩኒቨርሲቲ	X			
25	ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ	X	X	XX	XX
26	ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ	X	X	XX	X
27	ጎንደር ዩኒቨርሲቲ	X	X	X	X
28	ወሎ ዩኒቨርሲቲ	X	X	XX	X
29	ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ	X			
30	ትምህርት ሚኒስቴር	X			
31	አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X	XX
32	ወላይታ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X	X
33	ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ	X	XX	XX	
34	ዲላ ዩኒቨርሲቲ	X	X	XX	
35	ወሊጋ ዩኒቨርሲቲ	X			
36	አምቦ ዩኒቨርሲቲ	X			
37	ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ	X			
38	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X	X
39	አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ	X			
	የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች				
40	የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢኒስቲትዩት	X			

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	2008	2007	2006	2005
41	አሶሳ ዩኒቨርስቲ	x			
42	ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ	X			
43	ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ	X	XX	X	
44	ሳይንስና ቴክ.ሚኒስቴር	X			
45	ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ	X	X	XX	
46	የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	X			
47	የኢትዮጵያ የብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት	X	X		
48	አዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X	XX
49	አዲግራት ዩኒቨርሲቲ	X			
50	ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ	X			
51	ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ	X			
52	የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል	X			
53	የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ	X			
54	መቱ ዩንቨርስቲ	X			
	የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች				
55	የፌዴራልናአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር	X			
56	የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	X			
57	የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ	X			
58	የፌዴራል በጎ አደራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ	X			
59	የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን	X			
60	የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	X			
61	የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር	X	X	X	X

አባሪ - 3

የ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት ማሻሻያ ሀሳብ አተገባበር የድርጊት መርሃ ግብር እስከ ሚያዝያ 30/2009 የላኩ እና ያልላኩ መ/ቤቶች

ተ. ቁ.		የመ/ቤቱ ስም	መርሃ ግብር የላኩ	መርሃ ግብር ያልላኩ
		የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		
	1	የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል		x
	2	የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል		x
	3	የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት		x
1		የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት	x	
	4	የፍትህና የሕግ ሥርአት ምርምር ኢንስቲትዩት		x
	5	አሶሳ ዩኒቨርሲቲ		x
	6	ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ		x
2		ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ	x	
	7	ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር		x
3		ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ	x	
	8	የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር		x
	9	የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ		x
4		የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር	x	
	10	የኢትዮጵያ የብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት		x
	11	የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት		x
	12	የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ		x
5		የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን	x	
6		የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት	x	
	13	የምግብ መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት		x
	14	የብሔራዊ የቁላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት		x

ተ. ቁ.		የመ/ቤቱ ስም	መርሃ ግብር የላኩ	መርሃ ግብር ያልላኩ
	15	የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት		x
	16	የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል		x
	17	የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ		x
	18	መቱ ዩንቨርሲቲ		x
	19	የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የሥልጠና ማዕከል		x
	20	አዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ		x
	21	አዲግራት ዩኒቨርሲቲ		x
7		ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ	x	
	22	ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ		x
8		የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን	x	
	23	የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት		x
9		የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት	x	
10		የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	x	
11		ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ	x	
	24	የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር		x
	25	የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር		x
		የልማትና ማሕበራዊ መ/ቤቶች		
12		የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	x	
13		የኢትዮጵያ ምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን	x	
14		የማዕድን፣ ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር	x	
15		የትራንስፖርት ሚኒስቴር	x	
16		የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	x	
17		የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	x	
	26	የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ		x
18		የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	x	
19		የስትራተጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ	x	

ተ. ቁ.		የመ/ቤቱ ስም	መርሃ ግብር የላኩ	መርሃ ግብር ያልላኩ
	27	የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን		x
	28	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን		x
20		የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	x	
21		የአለርት ማዕከል	x	
22		የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን	x	
	29	የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር		x
	30	የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር		x
	31	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት		x
23		የብሄራዊ ደም ባንክ አገልግሎት	x	
	32	የኢትዮጵያ ጤና መድኅን ኤጀንሲ		x
	33	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን		x
	34	የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር		x
	35	የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ		x
24		ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	x	
		የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች		
25		ሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	x	
26		ምህራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	x	
		የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		
27		የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር	x	
	36	የብሔራዊ መረጃ ደህንነት አገልግሎት		x
	37	የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን		x
	38	የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት		x
	39	የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት		x
	40	የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ		x
	41	የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ		x
	42	የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር		x

ተ. ቁ.		የመ/ቤቱ ስም	መርሃ ግብር የላኩ	መርሃ ግብር ያልላኩ
	43	የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ		x
	44	የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ		x
	45	ንግድ ሚኒስቴር		x
	46	የፌዴራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር		x
	47	የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን		x
	48	የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ		x
	49	የበጎ አደራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ		x
	50	የኢትየጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን		x
	51	የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት		x
		የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት		
	52	ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ		x
28		ሠመራ ዩኒቨርሲቲ	x	
	53	ጅማ ዩኒቨርሲቲ		x
	54	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ		x
	55	ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ		x
29		አክሱም ዩኒቨርሲቲ	x	
	56	ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ		x
30		ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ	x	
31		ጎንደር ዩኒቨርሲቲ	x	
	57	ወሎ ዩኒቨርሲቲ		x
32		ትምህርት ሚኒስቴር	x	
33		አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	x	
34		ወላይታ ዩኒቨርሲቲ	x	
	58	ዲላ ዩኒቨርሲቲ		x
35		ወለጋ ዩኒቨርሲቲ	x	
	59	አምቦ ዩኒቨርሲቲ		x
	60	ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ		x

ተ. ቁ.		የመ/ቤቱ ስም	መርሃ ግብር የላኩ	መርሃ ግብር ያልላኩ
	61	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ		x
36		መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	x	
	62	አርሲ ዩኒቨርሲቲ		x
37		ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	x	
	63	የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ኤጀንሲ		x
	64	የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል		x
38		ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ	x	
		የፋይናንስና ኮሙዩኒኬሽን መ/ቤቶች		
	65	የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን		x
39		የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር	x	
40		የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት	x	
41		የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ	x	
	66	የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን		x
	67	የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት		x
	68	የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር		x
	69	የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር		x
42		የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት	x	
43		የመለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ	x	
	70	የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት		x
	71	የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስትቲዩት		x
44		የህብረት ስራ ኤጀንሲ	x	
	72	የወጣቶችና ስፖርት አካዳሚ		x
	73	የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት		x
45		የቤተ መንግሥት አስተዳደር	x	
46		የኢትጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ	x	
	74	የብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ		x
	75	የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ		x
	76	የብሔራዊ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት		x

ተ. ቁ.		የመ/ቤቱ ስም	መርሃ ግብር የላኩ	መርሃ ግብር ያልላኩ
	77	የፐሬዘዳንት ጽህፈት ቤት		x
47		የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን	x	
	78	የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት		x
48		የፌዴሬሽን ምክር ቤት	x	
	79	ብሔራዊ አደጋ ስጋትና ስራ አመራር ኮሚሽን		x
49		የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን	x	
50		ብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን	x	

አባሪ - 4

የ2008/9 ኦዲት ዓመት የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት የመርሃ ግብር እስከ ሚያዝያ 30/2009 የላኩ እና ያልላኩ መ/ቤቶች ዝርዝር

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	መርሃ ግብር የላኩ	መርሃ ግብር ያልላኩ
1	የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት	x	

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ቀድሞ ይገኝ ከነበረበት ፒያሳ አካባቢ በመልቀቅ ፍላሚንጎ አካባቢ ወደሚገኘው አዲሱ የመ/ቤቱ ህንጻ ከሰኔ ወር አጋማሽ 2008 ዓ.ም ጀምሮ ተዛውሯል፡፡





የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

ስልክ ቁጥር፡ +251115575701 ድረ-ገጽ www.ofag.gov.et

ኢ-ሜይል- ofagit@ethionet.et ፖ.ሳ.ቁ- 457

- Office of the Federal Auditor General, Ethiopia